# በትንቢት ግልጽ
# የተደረጉ ክስተቶች

አሁን ለጸሎት ራሳችንን ዝቅ እናድርግ። ሰማያትንና ምድርን የፈጠርክ ታላቅ ፈጣሪ፡ ኢየሱስን ከሙታን ዳግም ያስነሣኸው፡ ለእነዚህ ሁለት ሺህ ዓመታት ከእኛ ጋር ሕያው የሆንክ፡ ቃልህን ለማጽናትና ለእያንዳንዱ ትውልድ እውነት ለማድረግ፡ ዘወትር ሕያው የሆንክ ጌታ አምላካችን ሆይ። አሁን እዚህ ስላለው መለኮታዊ ህልውናው እጅግ አመስጋኞች ነን፡ ይህንንም እናውቃለን፡ ይኸውም ይህ ሕይወት ካለፈ በኋላ፡ በሚመጣው ዓለም የዘላለም ሕይወት እንዳለን፡ ይህ ታላቅ ማረጋገጫ አለን። ጌታ ሆይ፡ ስለዚህ፡ እናመሰግንሃለን። ይህም ተሰፋ፡ ለነፍስ እንደ መልህቅ፡ በማዕበል ጊዜ የጸናና አስተማማኝ ነው። ማዕበል ሲመጣም፡ ታላላቆቹ ሞገዶች ሲናወጡ፡ በእርሱ ባለን እምነት እያንዳንዱን ሞገድ በድል ማለፍ እንደምንችል ይሰማናል።

2 አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ማታ ለታመሙትና ለተቸገሩት ለማገልገል ስንመጣ እርዳን። አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ማታ ከዚህ ስንወጣ በመካከላችን አንድም የታመመ ሰው እንዳይኖር፡ እንጸልያለን። እዚህም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ፡ በሰልክ መስመር ላይ ያሉ ሁሉ፡ በመለኮታዊ ኃይልህ ይፈወሱ፡ ዛሬ ማታ ከማንኛውም ሕንፃ ወይም ከየትኛውም ስብሰባ አንድም ደካማ ሰው አይውጣ። መንፈስህ ይፈውሳቸው። ፈውስን በክንፎቹ የያዘው፡ ታላቁ የጽድቅ ፀሐይ፡ ይውጣ፡ እርሱ አሁንም በሕይወት እንዳለ የሚያሳምናቸውን የቅዱስ መንፈስ መገለጦች ሲመለከቱ፡ እና ቃሉን ሲያዳምጡ በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ የእምነት ጨረሮችን ይላክ። አባት ሆይ፡ እነዚህን በረከቶች፡ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

3 ዛሬ ምሽት እንደገና እዚህ ተገኝተን ለሕዝቡ ለመናገርና፡ ለሕሙማን፡ ለ—ለመጸለይ መቻላችንን በእርግጥም እንደ ታላቅ ዕድል እንቆጥረዋለን። ዛሬ ማታም እንደገና፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በ—በሰልክ ግንኙነት መስመር ውስጥ ያሉትን ሁሉ ሰላምታ ልናቀርብላቸው እንወዳለን። ስለዚህም ዛሬ ጧት ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞሉና፡ እዚህ ምድር ላይ ሕይወት እስኪያልፍ ድረስ ይኸውም ይህ ሟች ሕይወት እስኪያበቃ ድረስ ለእርሱ ታማኝና እውነተኛ ሆነው እንደሚኖሩ በማመን፡ እግዚአብሔር እያንዳንዳችሁን እንዲባርክ እንጸልያለን። ከዚያም፡ ይህንን በማድረጋቸው፡ የዘላለም ሕይወት አላቸው። በሚመጣው ዘመን፥ ሁላችንም በጉጉት ወደምንጠብቀው ታላቁ ዘመን ውስጥ ፈጽሞ አይሞቱም።

4 አሁን እያሰብኩበት ሳለ፡ ልናገረው የምፈልገው ነገር አለ፡ ላለማቋረጥ ያህል ነው። ወንድም ቬይል እዚህ ነው፡ ላላገኘው እችላለሁ። ወ... ወደ ቱክሰን ሰመለሰ ያንን ጽሑፍ ልልክልህ እችላለሁን? እያየሁት ነው፡ ገና ሁሉንም አንብቤ አልጨረሰኩትም፡ ወደ ቱክሰን እንደደረስኩም ወዲያው እመልስልሃለሁ።

5 አሁን አንድ ማስታወቂያ ማሳወቅ እፈልጋለሁ። ይህ በተለይ በየቦታው ላሉ ቤተክርስቲያናት ነው፡ በተለይም በምዕራብ ላሉት፡ ወይም መምጣት ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው ነው። የተከበረው ወንድማችን፡ ወንድም ፔሪ ግሪን፡ ከ... እዚህ ላለው የዚህ ሰልክ ግንኙነት ጠንሳሽ የሆነው ሰው ነው። ወደ ቱክሰን መጥቶ እንዲጎበኘንና እኛም በእውነት የሚያስፈልገንን፡ መነቃቃት በቱክሰን እንዲጀምር፡ ጌታ በልቡ ላይ ሲያስቀምጥበት ቆይቷል። ወንድም ፔሪም በቱክሰን ይሆናል። እርሱን ማግኘት ከፈለጋችሁ፡ እዚያ ያለውን ቢሮአችንን አናግሩ። ቀኑም ኦገስት 10፡ 11፡ 12፡ እንዲሁም 13 ይሆናል። ይህንንም ለረጅም ጊዜ በልቡ ውስጥ ይዞት ነበር፡ “ከልብህ የምታወጣበት ብቸኛው መንገድ፡ ሄደህ ማድረግ ብቻ ነው” ብዬ ነገርኩት። እርሱም ክርስቲያን ወንድም ነው፡ የእግዚአብሔር እውነተኛ አገልጋይ ነው። በቱክሰን ያላችሁ፡ እናንተም፡ እዚያ የሆነ ቦታ ምናልባትም በራማዳ ኢንን ሲያገለግል፡ ወይም ጌታ በሚያዘጋጀው በየትኛውም ስፍራ ሲያገለግል እንደምትባረኩ አውቃለሁ፡ እዚህ ላይ ሰፍራውን አልጻፈውም። ነገር ግን መጥታችሁ በመገኘት፡ ወንድም ግሪን የእግዚአብሔርን ቃል ሲያብራራልን በመሰማት፡ ምናልባትም ለታመሙት ሲጸልይ፡ ወይም የእግዚአብሔር ቅባት እንዲያደርገው በሚመራው በማንኛውም አገልግሎት እንደምትባረኩ አውቃለሁ።

6 ከእነርሱ ጋር ላሳለፍነው ለዚህ አስደናቂ የኅብረት ጊዜ ወንድም ኦርማን ኔቪልን፡ ወንድም ማንንም፡ ልናመሰግን እንወዳለን። እንደ ወንድም ኔቪል፡ ወንድም ማን፡ እንዲሁም እዚህ ዙሪያ ካሉት ሌሎች አገልጋዮች ሁሉ ጋር፡ ኅብረት በማድረጌና አብሬያቸው በመሆኔ ምንኛ አመስጋኝ ነኝ። ዕውቅና እንደተሰጣቸው እሰባለሁ። እዚህ ባለው ቦርዳችንና ቤተ ክርስቲያናችን፡ ዕውቅና ባታገኙም እንኳ፡ እግዚአብሔር አገልጋዮቹ እንደ ሆናችሁ እዚህ ዕውቅና እንደሚሰጣችሁ እርግጠኛ ነኝ። ጌታ ለዘላለም ይባርካችሁ።

7 አሁን፡ እዚህ አንድ ትንሽ ነገር ተጠይቄያለሁ፡ በተሰጠኝ አጭር ማስታወሻ ላይ፡ ወደ... በቀደም ምሽት እዚህ የባለአደራዎች ስብሰባ ነበራቸው፡ በባለአደራዎችና በዲያቆናት ቦርድ ዘንድ፡ ዛሬ ጧትም በቤተ ክርስቲያኒቱ ፊት ቃለ ጉባኤው የተነበበ ይመስለኛል። ይህም፡ ያንን ማድረግ ልማዳችን ነው። እዚህ በቤተ ክርስቲያኒቱ የባለአደራዎችና የዲያቆናት ቦርድ ባስተላለፈው ውሳኔ፡ በእርግጥ፡ ሁሉንም ሰው ማስደሰት አይቻልም። ያንን ማድረግ አንችልም። ከባለአደራዎች ቦርድ ወይም ከዲያቆናት ቦርድ ጋር የማደርገው አንዳችም ነገር የለኝም። ድምፅ እኩል ካልተከፈለ በቀር የድምፅ መብት እንኳ የለኝም፡ ያንንም ለማድረግ በወቅቱ እዚህ መገኘት አለብኝ፡ ከዚያም ወንድም ኦርማን ኔቪል ያንን ሁለተኛ ድምፅ ይወስዳል። የቤተ ክርስቲያኒቱ አካልም ስለሆንን፡ በእነዚህ ላይ መፈረም አለብን። ሆኖም የባለአደራዎች ቦርድና እነዚያ ቦርዶች የሚያሳልፉትን ውሳኔ፡ ከመቶ እጅ ከመቶ በእርግጥ እንደግፋለን፡ ምክንያቱም እዚህ ያሉት ለዚሁ ዓላማ ነውና። ውሳኔያቸውም በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ነው። በማንኛውም መንገድ፡ ያንን ውሳኔ ልቃወም አልችልም፡ አልችልምም፡ ፈጽሞም አላደርገውም። ሌላው ነገር ደግሞ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዓይነት ውሳኔ እንዳላሳልፍ በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ተከልክያለሁ፡ ስለዚህ እባካችሁ ውሳኔያቸውን እንዳስተካክል አትጠይቁኝ። ላደርገው አልችልም፡ ስለ ጉዳዩም ምንም አልሰማም። እያችሁ?

ስለዚህ ውሳኔያቸውን እንዳስተካክል አትጠይቁኝ። ቦርዱን ታነጋግራላችሁ፡ ውሳኔዎቹን ያሳለፈው እርሱ ነው። መልካም።

8 አሁን ስለሚመጣው ስብሰባ ሁኔታ ስንነጋገር፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ምናልባትም፡ ለሌላ የእሑድ ስብሰባ ከአራት እስከ ስድስት ሳምንታት ባለ ጊዜ ውስጥ፡ ወይም በዚያ አካባቢ፡ ወደዚህ ልመለስ እችላለሁ። ዛሬ ጧትም **እግዚአብሔር በቃሉ ተገለጠ** በሚለው ርዕስ ላይ ለመናገር እንደምፈልግ አሳውቄ ነበር፡ ዛሬ ማታ ግን ጊዜ አይኖረኝም፡ እውነቱን ለመናገር፡ ይህን ለማድረግ የሚያስችል፡ በቂ ድምፅ እንኳ የለኝም። ደግሞም ሕዝቡ፡ በውስጥ እንዳለው ሁሉ በውጭም ያን ያህል ቁጥር ያለው ሕዝብ አለ፡ ምናልባትም በውጭ ከሕዝቡ ጋር የቆሙትን አውቶቡሶችና፡ የጭነት መኪኖች እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን ስንቆጥር ከዚህም ሊበልጥ ይችላል። በርቶ፡ አነስተኛው ስርጭት ትንሽ ከፍ ብሏል፡ ልንሰማው እንችላለን፡ ይህን ትንሽ ሞገድ፡ ከተበርናክል የሚወጣውን አጭር ሞገድ፡ ከአንድ የከተማ ሰፈር ርቀት ላይ ሆነን ልንቀበለው እንችላለን። አንዳንዶቹ መኪኖች ጥቂት የከተማ ብሎኮች ያህል ርቀዋል፡ ዛሬ ማታ በተበርናክሉ ዙሪያ፡ የመኪና ስልፎች፡ ወደ ላይ እና ወደ ታች፡ እንዲሁም በመንገዶቹ ዙሪያና ውስጥ አቋርጠው ይገኛሉ። ዛሬ ማታ ካለው በላይ በማንኛውም ጊዜ፡ በዓይን በሚታይ ሁኔታ፡ ይህን ያህል ብዙ ሕዝብ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥና ዙሪያ ተጨናንቆ ያውቃል ብዬ አላምንም። ስለዚህ እኛ… እንዲሁም ብዙ፡ ብዙ፡ ብዙ ሰዎች መኪናቸውን እየነዱ መጥተው ተመልሰው ይሄዳሉ።

9 ስለዚህ ይህ፡ "ሬሳው ባለበት፡ ንስሮች ይሰበሰባሉ" የሚለውን ያሳያል። ዛሬ ማታ ልነግራችሁ የምችለው፡ በዚህች አነስተኛ የሰዎች ስብሰብ ውስጥ፡ ይህ ዓለም አቀፍ ጉባኤ መሆኑን ነው። በተግባር ከኅብረቱ ክፍለ አገራት፡ ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት እዚህ ተወክለዋል፡ ከአምስት የውጭ አገራት በተጨማሪ፡ እስከ ሩሲያ ድረስ፡ ከመላው አገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎችም ጭምር። ወደ ታች እስከ ቬንዙዌላ፡ ወደ ጃማይካ፡ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሁሉ፡ እግዚአብሔርን የተራቡና የተጠሙ፡ ሰዎች እዚህ ይገኛሉ። ምንኛ ድንቅ ጊዜ ነው!

10 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበቤ በፊት፡ እንድትጸልዩልኝ እፈልጋለሁ። ጌታ ቢፈቅድ፡ መለኮታዊ ፈውስን ስለ መቀበል፡ አጭር መልእክት ለ— ለማምጣት እሞክራለሁ። ምክንያቱም፡ ዛሬ ጧት ስለ መዳን ተነጋግረናል። ዛሬ ማታ ደግሞ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለ መለኮታዊ ፈውስ እንናገራለን፡ ከዚያም የጸሎት መስመሩን ጠርተን ለሕዝቡ እንጸልያለን። ይህንን እያደረግን ሳለ፡ በስልክ ግንኙነቱ ላይ ያላችሁ፡ የትም ቦታ ብትሆኑ፡ በተበርናክሉ ዙሪያ፡ በአንድ ወይም በሁለት ብሎኮች ርቀት ላይ ባሉ አውቶቡሶችና፥ መኪናዎች ውስጥ ያላችሁም ጭምር ለሕሙማን የምንጸልይበት ሰዓት ሲደርስ፡ ወደ ሕንፃው መግባት ካልቻላችሁ… ማለት፡ መግባት እንደማትችሉ፡ እርግጠኛ ነኝ፡ ምክንያቱም በየቦታው ያሉት መግቢያዎች በጣም ተጨናንቀዋል፡ የትም ቦታ ምንም የሚሆን ስፍራ የለም፡ ይልቅ፡ እዚያው እርስ በርሳችሁ እጆቻችሁን እየተጫጫናችሁ ጸልዩ። ዛሬ ማታ በስልክ የተገናኘ እያንዳንዱ አገልጋይም፡ የፈውስ አገልግሎቱ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ ለጉባኤው ይጸልይ። እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ፡ የሚገኝ አምላክ እንደሆነ እናምናለን። አሁን ከማንበባችን በፊት

ወይም...

11 ከ—ከመጸለያችን በፊት፡ ጥቂት የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ እንፈልጋለን። ከጥቂት ጊዜ በፊትም ጥ—ጥቅሶቼን ቀይሬአለሁ፡ ምክንያቱም ለዛሬ ማታ በአእምሮዬ አሰቤው የነበረውን የስብሰባ ዓይነት መቀየር ስለፈለግሁ፡ ስለዚህ ትንሽ ቀይሬዋለሁ፥ ስለዚህም ጥቅሶቼን መቀየር ነበረብኝ፡ እነርሱን መቀየር ሳይሆን፡ ሰዎች እንዲገባቸው በማለት፡ በመለኮታዊ ፈውስ ዙሪያ፡ በ—በሌላ ቅደም ተከተል ማዘጋጀት ነበረብኝ።

ወደ ቅዱስ ሉቃስ፡ 24ኛው ምዕራፍ እንግለጥ። ከ24ኛው ምዕራፍ 12ኛ ቁጥር ጀምረን፡ እስከ 34 አካባቢ እናነባለን። ይህም ስለ ጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ ነው።

> ጴጥሮስ **ግን፡ ተነሥቶ፡ ወደ መቃብር ሮጠ፥ በዚያም ዝቅ ብሎ ሲመለከት፡ የተልባ እግር ልብሰን ብቻ አየ... በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ ሄደ።**
>
> **እነሆም፡ ከእነርሱ ሁለቱ** በዚያ **ቀን፡ ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ፡ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር።**

አሁን፡ አንድ ማይል አ—አሥር ምዕራፍ ያህል ይወሰዳል፡ ስለዚህ ስድስት ማይል ያህል ነበር።

> **ስለዚህም** ስለ **ሆነው ነገር ሁሉ... እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።**
>
> **... እንዲህ ሆነ፡ ይህም፡ ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፡ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ፡ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር።**
>
> **ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር።**
>
> **እርሱም፡ እያዘናችሁ ስትሄዱ፡ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች፡ ምንድር ናቸው?**
>
> **ቀለዮጳ የሚባልም፡** አንዱ መልሶ፡ **እንዲህ አለው፡ አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን፡ በእነዚህ... ቀኖች በዚያ** የሆኑ እነዚያ **ነገሮች** አንተ **አታውቅምን?**
>
> **እርሱም፡ ይህ ምንድር ነው አላቸው?**

አሁን አስታውሱ፡ ይህ እየተናገረ ያለው፡ ራሱ ኢየሱስ፡ ተነስቶ ነው።

> **እነርሱም እንዲህ አሉት፡ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት፡ በሥራና** በ**ቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፥**
>
> **... እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን**... ለ—**ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና፡ እንደ ሰቀሉት ነው።**
>
> **እኛ ግን እሰራኤልን እንዲቤዥ ያለው** እርሱ **እንደ ሆነ ተሰፋ አድርገን ነበር፥ ደግሞም** ከዚህ **ሁሉ ጋር፡ ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።**
>
> **ደግሞም፡ ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት፡ አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፥**

**ሥጋውንም ባጡ ጊዜ፡ ሕያው ነው የሚሉ፡ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን፡ ሲሉ፡ መጥተው... ነበር።**

**ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው፡ ሴቶች እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙት፥ እርሱን ግን አላዩትም።**

አሁን አዳምጡ፥ ኢየሱስ።

**እርሱም፡ እናንተ የማታስተውሉ፡... ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፥**

**ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና፡ ወደ ክብሩ** ይገባ **ዘንድ ይገባው የለምን አላቸው?**

**ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ፡ ስለ እርሱ በመጻሕፍት** ሁሉ፡ **የተጻፈውን ተረጐመላቸው።**

ወደሚ**ሄዱበትም፡ መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው።**

**እነርሱ ከእኛ ጋር እደር፥ ማታ** ቀርቦአልና፡ **ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል፡ ብለው፡ ግድ አሉት። ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ።**

**እንዲህም ሆነ፡ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፡ እንጀራውን አንሥቶ፡ ባረከው፡ ቈርሶም፡ ሰጣቸው።**

ዓይናቸውም **ተከፈተ፡ አወቁትም፥ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ።**

**እርስ በርሳቸውም፡ በመንገድ ሲናገረን፡ መጻሕፍትንም ሲከፍትልን፡ ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን ተባባሉ?**

**በዚያችም ሰዓት፡ ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡ አሥራ አንዱን በአንድነት ተሰብስበው አገኙአቸው፡ ከእነርሱ ጋር** ሆነውም፡

**ጌታ በእውነት ተነሥቶአል፡** ለስምዖንም **ታይቶአል፡ አሉ።**

**እነርሱም በመንገድ የሆነውን፡ እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ** እንዴት **እንደ ታወቀ**ላቸው **ተረኩላቸው።**

12 አሁን እንጸልይ። ውድና ጸጋ የሞላብህ አባት ሆይ፡ ስለ ቃልህ እናመሰግንሃለን፡ ቃልህ እውነት ነውና፡ ቃልህ ሕይወት ነውና። ኦ ጌታ ሆይ፡ አንተና፡ ቃልህ አንድ ናችሁ። ስለዚህ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በትንሣኤህ ኃይል በመካከላችን እንድትመጣና ዛሬ ማታ እንድትገለጥልን እንጸልያለን፡ ከኤማሁስ እንደመጡት እነዚያ ሰዎች፡ እኛም ወደ ቤታችን ስንመለስ፡ "ልባችን በውስጣችን ይቃጠል አልነበረምን? " እያልን እንድንመለስ አድርገን፡ ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ፡ ዳግመኛ ወደ ምሽት ጊዜ እየተቃረበ ነውና። በኢየሱስ ስም እንለምናለንና። አሜን።

13 አሁን ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መናገር እፈልጋለሁ። ዛሬ ማታ ለሀሳቤ የምሰጠው፡ ርዕሴ፡ **በትንቢት ግልጽ የተደረጉ ክስተቶች፡** የሚል ነው። **በትንቢት ግልጽ የተደረጉ ክስተቶች።**

14 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ቅዱሳን መጻሕፍት ሁሉ የተለየ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ መጽሐፍ ነው። እርሱ ወደፊት የሚሆኑትን

ክንውኖች፡ አስቀድሞ የሚናገር የትንቢት መጽሐፍ ነው። ደግሞም የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ፡ እርሱ ምን እንደ ነበረና ምን እንደሆነ፡ በሙላቱ አውጥቶ ያሳየዋል። ሙሉውም መጽሐፍ፡ በራእይ 1፥1 እስከ 3 ላይ እንዳለው፡ መጽሐፉ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው "የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡" መጽሐፍ መሆኑን ይናገራል። "የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡" የእግዚአብሔር ቃል!

15 አሁን፡ ሌሎች መጻሕፍት ሁሉ፡ ቅዱሳን መጻሕፍት፡ የሥነ ምግባር ደንብ፡ የሞራል ደንብ፡ ወይም የሰነ መለኮት ደንብ ብቻ ናቸው። የሆነ ነገር... ቁርኣንን፡ የሙስሊሞችን መጽሐፍ፡ እ—እንዲሁም የቡድሂስቶችን መጽሐፍና፡ የመሳሰሉትን ያነበባችሁ ስንት ናችሁ? የሥነ ምግባር ደንብ ብቻ ነው፡ ሰዎች ምን መኖር እንዳለባቸው፡ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ይናገራል፡ ነገር ግን ትንቢት አይናገርም፡ ስለ እነዚህ ነገሮች ወይም ለማንም ስለሚሰጡ ልዩ ስጦታዎች፡ ስለሚፈጸም ማንኛውም ነገር አንዳችም አይናገርም። ልክ ማኅበርን ወይም ሌላን ነገር እንደ መቀላቀል ያህል ነው። ስለዚህ፡ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመቀላቀል እንደ ማኅበር ብቻ ወደሚያደርጉበት ደረጃ ሲደርሱ፡ ያኔ ከእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ ወጥተዋል።

16 መጽሐፍ ቅዱስ ሕያውና፡ አስቀድሞ የተነገረ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ነውና። ምድርም ወደ ሙሉነቷ እንዳደገች፡ ወይናችም ወደ ሙሉነታቸው እንደሚያድጉ፡ ቀንም ወደ ሙሉነቱ እንደሚያድግ፡ መጽሐፍ ቅዱስም በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በሙላቱ ተገልጧል። እርሱ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል፡ ሙሉውና ፍጹሙ የቤዛነት መጽሐፍ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት የሚሆኑ ነገሮች፡ አስቀድሞ የሚናገርበት የእግዚአብሔር ቃል ነው። አማኞች ከፊሉን ብቻ ሳይሆን፡ እያንዳንዱን ቃል እንዲያነቡና እንዲያምኑ በደራሲው ታዝዘዋል። አንዱን ቃል፡ ላለማመን፡ ያንን ቃል እስክታምኑ ድረስ መሞከራችሁን ብታቆሙ ይሻላል። እያንዳንዱ ቃል በእርግጠኝነት የሁሉን ቻይ አምላክ አካል ነው፥ እርሱ ማን እንደሆነ ለማሳየት፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ በቃሉ ውስጥ ተጠቅልሎ ተገልጧል። እኛም አማኞች እንደ መሆናችን መጠን፡ እያንዳንዱን ቃል እንድናምን፡ ታዝዘናል። እርሱም የተጻፈው በደራሲው በራሱ በእግዚአብሔር ነው። በእርሱ ላይ ምንም መጨመርም ሆነ ከእርሱ ላይ ምንም መቀነስ የሚችል ማንም የለም። ብታደርጉት ኖሮ፡ የተዛባ የእግዚአብሔር አካል ይሆን ነበር። አንድን ነገር መጨመር ማለት፡ ምናልባት በአንድ እጅ ላይ ስድስት ጣቶች፡ ወ—ወይም ሦስት ክንዶች፡ ወይም ሌላ ነገር እንዲኖረው ማድረግ ማለት ነው፡ ከእርሱ አንድን ነገር መቀነስ ደግሞ፡ አንድ ክንድ ማሳነስ፡ አንድ ጣት ማሳነስ ማለት ነው። እርሱ ፍጹም የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ነው። ክርስቶስም፡ ወንድ፡ ሙሽራው እንደ መሆኑ መጠን፡ ሙሽራይቱም በእርሱ ውስጥ ተወክላለች። እነዚህም ሁለቱ አንድ ናቸው። "በዚያ ቀን እኔ በአብ ውስጥ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ ውስጥ እንዳለ፡ እኔም በእናንተ ውስጥ እንዳለሁ እናንተም በእኔ ውስጥ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።" ምንኛ ፍጹም የሆነ ምስል ነው!

17 የዚህ ቃል እውነተኛ አማኞችም፡ ቃሉን በዚህ መንገድ የሚቀበሉትና፡ የሚያምኑበት ሲሆኑ፡ ትንቢት የተነገረላቸው እያንዳንዱ ተሰፋዎቹም፡ በየዘመናቸው ይገለጡ ዘንድ በትዕግስት ይጠብቃሉ። እያንዳንዱ አማኝም

ይህን ሲጠባበቅ ኖሯል። በንቃት ሲጠባበቅ የነበረው፡ እያንዳንዱ አማኝም፡ ይህ የተገለጠለት ነው።

18 አሁን በጌታ በኢየሱስ መምጣት ቀናት የነበረውን ተመልከቱ። መጽሐፍ ቅዱስ በኢሳይያስ በኩል በግልጽ እንዲህ እየተናገረ፡ ሰዎች ዮሃንስን ማወቅ እንዴት ከበዳቸው፡ “በምድረ በዳ፡ ‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ’ ብሎ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ይሆናል”? የተላከላቸው የመጨረሻው ነቢያቸው፡ ይኸውም ሚልክያስ በምዕራፍ 3 ላይ “እነሆ፡ መንገድን እንዲያዘጋጅ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ፡” ብሎ ነበር። ይህስ ለምን አላዩትም? ምክንያቱም አስቀድሞ በተደረገው ነገር ላይ ይመለከቱ ስለነበር ነው፡ አሳባቸውንም ቀደም ብሎ በወጣው መልእክት ላይ በመመሥረት፡ በዚያ በሚኖሩበት ዘመን የነበረውን የአሁኑን የእግዚአብሔርን መገለጥ ማየት ተሰኗቸው ነበር።

19 በሁሉም ቦታ ያላችሁ፡ ክርስቲያኖች ሆይ፡ ዛሬ ማታ ዓለም የቆመበት ሁኔታ ልክ እንደዚሁ ነው። ያለ ምንም ጥርጥር፡ እውነቱ ይህ ነው! በየቦታው ያሉት፡ ክርስቲያኖች፡ ሰዎች በየቦታው የጻፏቸውን የ ሥነ ምግባር ደንብ ለመመልከት ይሻሉ ሚስተር ሉተር እንደጻፈው፡ ወይም ሚስተር ዌስሊ፡ ሳንኪ፡ ፊኒ፡ ኖክስ፡ ካልቪን፥ ይህም፡ ስለ እነርሱ ክፉ መናገር ባንችልም፡ ሆኖም ግን ያ ባለፈው ዘመን የነበረ ነው።

20 ፈሪሳውያን ሙሴ የተናገረውን ለማየት ወደ ኋላ ተመለከቱ፡ እንዲህም አሉ፡ “እኛ ሙሴ አለን። አንተ ግን ከወዴት እንደ መጣህ አናውቅም” አሉ።

21 ነገር ግን አስታውሱ፡ ሙሴ እዚህ በነበረበት ጊዜ፡ ከየት እንደ መጣ አላወቁም። አያችሁ? አሁንም እነርሱ... ኢየሱስ፡ “የነቢያትን መቃብር ታስጌጣላችሁ፡ በዚያም ያኖራችኋቸው እናንተው ናችሁ” ማለቱ ምንም አያስገርምም። መልእክታቸው ካለፈ በኋላ! አንድ መልእክት ይመጣል፡ ሰዎቹም ያዩታል፡ ያፌዙበታል (ዓለም ይህን ያደርጋል)። ከዚያም መልእክተኛው ካበቃና መልእክቱ ከተፈጸመ በኋላ፡ በመልእክቱ ላይ የሐይማኖት ተቋም ይገነባሉ። በዚያውም ይሞታሉ፡ ልክ እዚያው፡ ዳግመኛም ወደ ሕይወት አይመለስም።

22 ለአንዳንዶቻችሁ፡ በተለይም ለካቶሊክ እምነት ተከታዮች የምናገረውን፡ ለጥቂት ጊዜ ተመልከቱ። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ታሪክ፡ ታሪኩን አንብባችሁ ታውቃላችሁን፡ ተገንዝባችኋልን? በሰማዕታት መዝገባችሁ ላይ፡ ከሂፖው ቅዱስ አውግስጢኖስ ጀምሮ፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሰንት ሚሊዮን ንጹሐን ሰዎችን እንደገደለች ታውቃላችሁ! ረሳሁት፡ ትክክለኛውን ቁጥር ልጠራው አልችልም፡ ነገር ግን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ነው፡ በአፍሪካው፡ የሂፖ ቅዱስ... የሂፖው ቅዱስ አውግስጢኖስ-... የሮማ፡ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃወም ማንኛውንም ሰው መግደል ፈጽሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብሎ ካወጀበት ጊዜ ጀምሮ ብዙዎች ተገድለዋል። በዚህም ውስጥ፡ ቅዱስ ፓትሪክ ከሞተ በኋላ እንጂ፡ እንደ ሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታይ ሆኖ ዕውቅና አግኝቶ እንደማያውቅ ትገነዘባላችሁን? እርሱ ጳጳሱንና ድርጊቶቹን ሁሉ ተቃወመ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ራሷ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ልጆቹን ገድላለች። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያችን ቅድስት የሆነች ምስኪን ሴት፡ ጆአን ኦፍ አርክን፡ በግንድ አስራ እንዳቃጠለቻት ታውቃላችሁን፡ ይህም-... መተተኛ ናት

አለቻት። ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ፡ ስህተት መሆኑን ሲያውቁ፡ የካህናቱን አስከሬን ቆፍረው በማውጣት፡ ንስሐ ለመግባት ሲሉ፡ በተቀደሰ መሬት ውስጥ ሳይቀብሯቸው፡ ወደ ባሕር ጣሏቸው።

ዘመኑ ሳታስተውሉት በላያችሁ ላይ እንዲያልፍ አትፍቀዱ፡ ሞኞችም አትሁኑ።

23 ኢየሱስን የኮነኑት፡ እነዚያ ካህናት፡ ዛሬ ማታ፡ ወደ ፊት መምጣት ምንኛ ይመኙ ይሆን። ብቸኛው ነገር፡ የዚያን ዘመን ትንቢት ፈጽሞ አላዩም ነበር። እነርሱ... ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡ ለዚያች ሰዓት "መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ፡ በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁ፡" ወይም፡ ይልቁንስ፡ "እንዳላችሁ ትናገራላችሁ፡ እኔም ማን እንደሆንኩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሯችኋል፡" አለ።

24 አስተውሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሊወድቅ አይችልም። የእግዚአብሔር ቃል ሊያደርገው የማይችለው አንድ ነገር ቢኖር፡ መውደቅ ነው፡ ምክንያቱም ደራሲው ከማድረጉ በፊት ድርጊቶቹን አስቀድሞ ይነግራልና።

25 አሁን፡ አንድ ሰው አንድ ነገር እንደሚከሰት ትንቢት ቢናገር ያም የሚፈጸምበት አጋጣሚ፡ ከአንድ ሺህ አንድ እጅ የመሆን ዕድል ይኖረዋል። ነገር ግን **የሚከሰትበትን** ስፍራ ከወሰነ፡ ያ ዕድሉን ምናልባት ከአሥር ሺህ አንድ እጅ ወደ መሆን ዝቅ ያደርገዋል። የሚሆንበትንም **ቀን** ከተናገረ፡ ያ ደግሞ ዕድሉን ወደ አንድ ሚሊዮን፡ ዝቅ ያደርገዋል። **በማን** ላይ እንደሚሆንም ከተናገረ፡ ያ ዕድሉን ወደ ቢሊዮኖች ያወርደዋል።

26 ነገር ግን ይህ መጽሐፍ ቅዱስ **ማን፡ መቼ፡ የትና፡ ምን** መፈለግ እንዳለባችሁ በትክክል ይነግራችኋል፡ አንዴም እንኳ ወድቆ አያውቅም። ስለዚህ፡ በቅርብ ጊዜ፡ እዚህ አቅራቢያ ካለ የሴክሬድ ሃርት ቤተ ክርስቲያን ቄስ ጋር በነበረን አነስተኛ ውይይት ላይ፥ እንዲህ አለ፡ "አቶ ብራንሃም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ልትከራከር እየሞከርክ ነው።" እንዲህ አለ፡ "ያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነው" አለኝ።

እኔም፡ "ታሪክ አይደለም። በጽሑፍ የሰፈረው፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ነው" አልኩት።

እርሱም፡ "እግዚአብሔር ያለው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ነው" አለ።

27 እኔም እንዲህ አልኩት፡ "እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ነው። ከእርሱ የሚቃረን ማንኛውም ነገር፡ ደግሞ ውሸት ይሁን። እርሱም፡ 'የእኔ ቃል እውነት ይሁን የሰው ሁሉ ቃል ግን ውሸት ይሁን' ብሏልና።"

እርሱም፡ "መከራከር የለብንም" አለ።

28 እኔም፡ "እንድንከራከር ፈጽሞ አልጠየቅሁህም፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፡ 'ኑ፡ አብረን እንማከር' ይላል" አልኩት።

29 ደራሲው ከማድረጉ በፊት ድርጊቶቹን አስቀድሞ ይነግራል። ስለዚህ፡ ያንን መናገሩ፡ እያንዳንዱን ወንድና ሴት ያለምንም ማመካኛ በፍርድ ወንበር ፊት ያቆማቸዋል። ሜቶዲስቶች ስለ እርሱ የሚሉትን፡ ባፕቲስቶች ስለ እርሱ የሚሉትን፡ ካቶሊኮች የሚሉትን፡ ጴንጤቆስጤዎች የሚሉትን፡ ወይም ሌላ ማንኛዋም ቤተ ክርስቲያን የምትለውን ከወሰዳችሁ፡ በፍርድ ቀን የልብ ሰብራት

ሊያጋጥማችሁ ይችላል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናል ብሎ የተናገረውን ብቻ ከተመለከታችሁና፡ ያም ሲሆን፡ ያኔ የሆነውን ነገር ታውቁታላችሁ።

30 አሁን፡ ሁሉም ሰው ሊያየው በሚችልበት ሁኔታ በግልጽ የተቀመጠ አይደለም፡ ኢየሱስ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ስለሰወረው እግዚአብሔርን አመሰግኗልና፡ ነገር ግን ለመማር ፈቃደኛ ለሆኑት ሕፃናት ይገልጠዋል። ሁሉን ቻይ አምላክ በራሱ ቃል ውስጥ ሆኖ፡ ሀብታሞችን ትዕቢተኞችንና የ—የተማሩ ምሁራንን፡ እርሱን ማየት እንዳይችሉ ዓይኖቻቸውን በማሳወር፡ የድሆችንና ያልተማሩትን ዓይኖች ግን ሲከፍት አስቡት።

31 እነዚህን ከኤማሁስ የነበሩትን ሰዎች አስተውሉ፡ እርሱን የ—የማወቅ ማስተዋላቸው እንደ ተከለከለ ተናግሯል። ቀኑን ሙሉ ሲያነጋግሩት ውለው፡ ማን እንደ ሆነ እንኳ አላወቁም። እግዚአብሔር አምላክ ነውና፡ ያንን ሊያደርግ ይችላል።

32 በእነዚያ ካህናትና፡ በእነዚያ ጻፎች ላይ ያደረገውም ልክ ይህንኑ ነው፡ ምክንያቱም ያንን ማድረግ እንዳለበት ተጽፎ ነበርና። እኛ ዕድል እንድናገኝ እግዚአብሔር ዓይኖቻቸውን አሳወረ። አስተውሉ፡ ማየት አልቻሉም ነበር፡ ምንም ያህል ምሁራን ቢሆኑ፡ ምንም ያህል ካህናት ቢሆኑ፡ ምንም ያህል ያደረጉት ነገር ቢኖርም፡ ዕውሮች ስለ ነበሩ፡ አሁንም ሊያዩት አልቻሉም። በአካል ሲታይ፡ ዕይታቸው 20/20 ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን መንፈሳዊ ዕይታቸው!

33 ዛሬ ጠዋት ስለ ሴቶች ዝሙት፡ አሁን በሚለብሱት የአለባበስ ሁኔታ ላይ ልናገረው የሞከርኩትም ይኸው ነው። አመንዝራዎች ናቸው። በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የፍትወት ስሜት-ቀስቃሽ ልብሶችን በለበሱ ቁጥር በዝሙት ጥፋተኞች ናቸው። ነፍሳቸው፡ ይህን ሳታውቀው ነው። እነዚያ ሴቶች፡ ብዙዎቹ፡ በሺዎች የሚቆጠሩት ንጹሐን እንደሆኑና፡ በማንኛውም መንገድ፡ ዝሙት እንደማይፈጽሙ አምናለሁ። እነዚያም ምስኪን ሴቶች፡ ስሕተታቸውን ሳይገልጥላቸውና እውነቱን ሳይነግራቸው፡ ዝም ብለው ስለሚያልፏቸው፡ በዝሙት ላይ ይወድቃሉ። ይህም፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው፡ "በብዙ ውኃዎች ላይ የተቀመጠችው ጋለሞታ፡ የምድር ነገሥታትና የምድር ሕዝብ ሁሉ፡ አብያተ ክርስቲያናትና የመሳሰሉት፡ ከእርሷ ጋር መንፈሳዊ ዝሙትን ፈጽመዋል። እርሷም **የጋለሞታዎች እናት** ነበረች፡" ይኸውም የሐይማኖት ተቋማት ናቸው።

34 እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ አይተወንምና፡ መጽሐፍ ቅዱስን እንመለከታለን። ነገሮች ከመሆናቸው በፊት፡ እንዲሁም የሚመጡበትን ትክክለኛ ባሕርይና ጊዜ አስቀድሞ ሊነግረን መጽሐፍ ቅዱስን ልኳል።

35 አሁን፡ ይህ ቀኑ ሰንት እንደሆነ ለማየት የቀን መቁጠሪያን እንደ መመልከት ነው። ዛሬ ቅዳሜ ነው፡ ወይስ እሑድ ነው፡ ምንድን ነው፡ ብላችሁ ብታስቡ? የቀን መቁጠሪያውን ተመልከቱ። የቀን መቁጠሪያው ቀኑ ምን እንደሆነ ይነግራችኋል። የሰዎቹን ድርጊቶች ስታዩ፡ ምናልባት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ፡ ስታዩ—የ... ደወሎች ሲደወሉ ስትሰሙ፡ ቀኑ ምን እንደሆነ ትገረማላችሁ። የቀን መቁጠሪያውን ተመልከቱ፡ ቀኑ ምን እንደሆነ ይነግራችኋል።

36 ቤተ ክርስቲያንም በሰዶም ዘመን እንደነበረው ዓለማዊ ስትሆን ስታዩ፡ የቤተ ክርስቲያን ዓለም ሁሉ ወደ... "የዚህን የክፉ ዘመን አምላክ፡" ለማምለክ

ሲሄዱ ስታዩ፡ ያንንም አይታችሁ፥ ከዚያም በእግዚአብሔር መንፈስ ተነሳስተው ተለይተው የተሰበሰቡ ጥቂት ሰዎችን ስታዩ፡ መሆን እንዳለበት በሚናገረው መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ዳግም ሲያፈሩ ስታዩ፡ በየትኛው ዘመን ውስጥ እየኖራችሁ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።

37 ይህ መጽሐፍ ቅዱስ፡ በየትኛው ዘመን እንደምንኖርና፡ በየትኛው ጊዜ ውስጥ እንደምንኖር፡ እንዲሁም ምን ዓይነት ነገሮች መፈጸም እንዳለባቸው፡ በትንቢት አስቀድሞ ይነግረናል። በፊደል ደረጃ በትክክል አስቀድሞ ይናገረዋል፡ በሁሉም ጊዜ፡ አንዱንም ዘመን ስቶ አያውቅም። አንዴም እንኳ ስቶ አያውቅም፡ አይስትምም፡ ምክንያቱም እንዲያዩት አስቀድሞ የተወሰኑት ያዩታልና። ኢየሱስ፡ “አባቴ ከሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም፡ አብ የሰጠኝም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል” ብሏል። ይኸውም ቃሉ ከቃሉ ጋር መጣመር ነው። ሌላ ምንም ሊያደርግ አይችልም። የምንኖርበትን ቀን፡ እናውቀዋለን።

38 ነገር ግን በየዘመናቱ እንደነበረው፡ ሰዎች የራሳቸውን ትርጓሜ በዚህ ቃል ላይ እንዲያደርጉ ስለፈቀዱ፡ ለተፈጸመው ነገር ዓይኖቻቸው እንዲታወሩ አድርጓቸዋል። በፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም ላይ ያደረገው ይኸው ነው። ጳውሎስ እዚያ ቆሞ መጽሐፍ ቅዱስን ለመጥቀስ በሞከረበት ጊዜ እንኳ፡ ሊቀ ካህናቱን በኖራ የተለሰነ ግድግዳ ብሎ ሰለ ጠራው አንድ ሰው ፊቱን በጥፊ መታው። ከዚያም እግዚአብሔር ትንቢት የተነገረለትን ቃሉን ሲያጸና ከማየት ጎደሉ።

39 አያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን አይቃረንም፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ቅራኔ የለም፥ እርሱ ፍጹም ነው።

40 ነገር ግን ሕዝቡ፡ በገዛ ትርጓሜያቸው! አሁን አስተውሉ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ላሳያችሁ። አብያተ ክርስቲያናት ስለ ትርጓሜው እርስ በርሳቸው ሊስማሙ አይችሉም። ሜቶዲስቶች ከባፕቲስቶች ጋር፡ ባፕቲስቶች ከፕሬስባይቴሪያን ጋር፡ ፕሬስባይቴሪያን ደግሞ ከጴንጤቆስጤዎች ጋር ሊስማሙ አይችሉም። እንዲሁም ጴንጤቆስጤ ወደ አርባ በሚጠጉ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ሆኖ፡ እርስ በርሳቸው ሊስማሙ አይችሉም። ስለዚህ አያችሁ፡ ያ ዳግመኛ ባቢሎን፡ ግራ መጋባት ይሆናል።

41 ነገር ግን እግዚአብሔር የራሱን ቃል ራሱ ይተረጉመዋል። ይህንን ነገር ተስፋ ሰጠ፡ ከዚያም ራሱ ያደርገዋል። በዚያች ዘመን ራሱን ስለሚያሳውቅ፡ ትርጓሜውን፡ ራሱ፡ ይሰጠዋል። የክርስቶስ አካል ከ—ከእግር እስከ ራስ፡ ምን ያህል ወደ ፊት ገፍቷል!

42 አስተውሉ፡ እንግዲህ እነዚህ ሰዎች ይህንን ሊያገኙ ያልቻሉበት ምክንያት ይኸው ነው፡ ምክንያቱም ኢየሱስ እንዲያደርጉ እንደነገራቸው ቃሉን ከማንበብ ይልቅ፡ ሌላ ሰው ስለ ቃሉ የሚለውን ይሰማሉና፡ “ስለ እኔ የሚመሰክሩትም እነርሱ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ፡ በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁና፡ ስለ እኔ የሚመሰክሩትም እነርሱ ናቸው።” በሌላ አነጋገር፡ አዳምጡ፡ “ምን? መጽሐፍ ቅዱስን አንብቡና መሢሑ ምን ማድረግ እንደ ነበረበት ተመልከቱ። መሢሑ በየትኛው ዘመን መምጣት እንደ ነበረበት ተመልከቱ። ለመሢሑ መንገድ ጠራጊ የነበረው ማን እንደ ሆነ ተመልከቱ።

ሰዓቱን ተመልከቱ። በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ይሆናል፡ ዮሐንስ። እናንተም የወደዳችሁትን ሁሉ በእርሱ ላይ አደረጋችሁበት። ሰመጣ ምን ማድረግ እንደ ነበረብኝ ተመልከቱ። አሁንስ ምን አድርጋችኋል? ይህን ማሟላት ተሰኖኛልን?" አያችሁ፡ ኢየሱስ እየተናገረ ነው፡ "ይህን ማሟላት ተሰኖኛልን?"

43 አስተውሉ፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስናልፍ፡ ስለ እርሱ ትንቢት የተነገረው ሁሉ መሆን በነበረበት መንገድ በትክክል እንዴት እንደተፈጸመ እናያለን። ይህንን ነገር ማወቅ ነበረባቸው። "ይህ አክራሪ የሆነ፡ ወጣት ተነሳ፡ ሠላሳ-ሦስት ዓመት ገደማ የሚሆነውና... ወይም ሠላሳ ዓመት የሆነው፡ ወደዚያ ወርዶ ስለ ልዩ ልዩ ብርሃናትና፡ ስለሚወርዱ ርግቦች ተናገረ። አያችሁ፡ ይህ፡ ው—ውርደት ነበር።" እነርሱም፡ "ከሕገ ወጥ ወላጆች ተወልዶ፡ ከድንግል እንደ ተወለደ ይናገራል" አሉ።

44 ኢሳይያስ በኢሳይያስ 9፥6 ላይ፡ "ሕፃን ተወልዶልናል" እንዳለ፡ ማወቅ አልነበረባቸውምን? ነቢዩ ኢሳይያስ፡ "ድንግል ትፀንሳለች" እንዳለም ማወቅ አልነበረባቸውምን? እነዚህን ነገሮች ማወቅ ነበረባቸው። ሆኖም ግን፡ አያችሁ፡ ነገሩ ይህ ነው፡ እነርሱ ይህንን ወደ ፊት ለሚመጣ ሩቅ ጊዜ ይጠብቁት ነበር። ለእነርሱም፡ ይህ ሰው፡ መስፈርቱን አላሟላም። ነገር ግን እርሱ፡ "መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ፡ በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁና፡ ለመልእክቴም የሚመሰክሩት እነርሱው ናቸው" ብሎ ጠየቃቸው። አንዳንድ የሰነ መለኮት ምሁራን ያሉትን ሳይሆን፥ ነገር ግን እግዚአብሔር፡ የራሱ ቃል፡ ይሆናል ያለውን ነው! አሜን!

45 አሁንም ልክ እንደዚሁ ነው! መጽሐፍትን መርምሩ፡ ምክንያቱም የምንኖርበትን ዘመን የሚነግረን እርሱ ነውና፡ በዚህ ዘመን በትክክል ምን እንደሚሆን ይነግረናል። ልትደገፉበት የሚገባው እርሱ ነው፡ ምክንያቱም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የሚመሰክረው እርሱ ነውና። መጽሐፍ ቅዱስም፡ "እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡" ብሏልና፡ ምክንያቱም እርሱ በዘመኑ ያለው የቃሉ መገለጥ ነውና። የተለየ ሊሆን አይችልም።

46 ስለዚህ የሰውን ትርጓሜ በማዳመጥ፡ የእግዚአብሔር ቃል ተፈጽሞ ሲጸና ቢያዩም እንኳ፡ ማስተዋል ተሰኗቸዋል። ምክንያቱም፡ ይህ ሁልጊዜ እየሆነ ያለ ነገር ነው፡ ዳሩ ግን እነርሱ ስለሚያዳምጡ... ኢየሱስም፡ "እነርሱ ዕውር መሪዎች ናቸው" ብሏል። ዕውርም ዕውርን ቢመራው፡ ምን ይደርስባቸዋል? አሁን አስታውሱ፡ የዚህ የሎዶቅያ ዘመን የሆነው ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ዕውር እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ተናግሯል። እርሱን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ አድርገውት ነበር። ኢየሱስ በውጭ የነበረበት፡ ሌላ ዘመን፡ ሌላ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የለም። ነገር ግን በሎዶቅያ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ እርሱ በውጭ ሆኖ፡ ዳግመኛ ወደ ውስጥ ለመግባት እየሞከረ፡ "በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ" እያለ ነበር። እርሱ በውስጥ መሆን ነበረበት። ነገር ግን እርሱ እንዲህ አለ፡ "'ሀብታም ነኝ፡ በንብረትም በዝቻለሁ፡ አንዳችም አያስፈልገኝም፡' ስለምትል፡ ነገር ግን ዕውር፡ ዕውርንም የምትመራ፡ በመንፈስ ድሀ፡ ጐስቋላ፡ ምስኪን፡ ዕራቁትህንም እንደሆንክ፡ ስለማታውቀው ነው።" ይህ እንዴት ያለ ሁኔ-... አንድ ሰው በመንገድ ላይ ዕራቁቱን ቢሆን፡ ምስኪንና፡ ዕውር ቢሆን፥ ደግሞም ዕራቁቱን እንደሆነ ስትነግሩት የሚረዳበት በቂ አእምሮ እንዳለው ቢያውቅ ኖሮ፡ ስለ ጉዳዩ የሆነ ነገር ለማድረግ ይሞክር ነበር። ነገር ግን

ራሱን ነቅንቆ፡ እንዲህ ይላል፡ “ይህን አልቀበልም። ምን ማድረግ እንዳለብኝ የምትነግረኝ አንተ ማን ነህ? የት እንደ ቆምኩ አውቃለሁ።” አሁን፡ ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ካልሆነ፡ ሌላ ምን እንደሆነ አላውቅም። ደግሞም የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ አሁን ባለንበት በዚህ ክፉ ዘመን፡ በምንኖርበት በዚህ የመጨረሻ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደዚህ እንደምትሆን የተናገረው በትክክል ይኸው ነው።

47 አስተውሉ፡ ነገር ግን ለሰዎች፡ “እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻለሁ፡” ብሏል። አሁን፡ ስለምታደርጉት ነገር፡ በጌታ ከተገሠጻችሁ፡ ከእርሱ ውጡ! ከእርሱ ራቁ። “የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻለሁ።”

48 አሁን፡ እግዚአብሔርን በማየት፡ አሁን፡ እነዚያ ፈሪሳውያን፡ “ቆዩ። ያ ሰው ትልቅ ቻሌንጅ ሰጥቶናል፡ እንዲህ አለ፡ ‘መጽሐፍ ቅዱስን ትመረምራላችሁ፡ በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁና፥ እነርሱ ስለ እኔ ይመሰክራሉ።’ ወደ ኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመልክቼ ምን ማድረግ እንዳለበት፡ እርሱ ማን እንደ ሆነ፡ ምን መሆን እንዳለበት ብመረምር ይሻላል። ወደ ኋላ ተመልክቼ ላጣራ ይገባኛል” ቢሉ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? ከዚህ ይልቅ፡ ወደ ካህናቱ ሄደው “ስለዚህ ነገርስ ምን ትላላችሁ፡” ብለው ጠየቋቸው? ልዩነቱን አያችሁን? ቃሉን ማንበብ ነበረባቸው።

49 በዕብራውያን 1:1 ላይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “እግዚአብሔር፡ ከጥንት ጀምሮ፡” ያም ማለት፡ “በቀድሞ ዘመናትና በልዩ ልዩ መንገድ በመናገር መጽሐፍ ቅዱስን በነቢያት በኩል ጻፈ።” አሁን አስተውሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እርሱ ራሱ በመረጠው መንገድ ነው። አያችሁን? አሁን፡ በዚያ መንገድ መጻፍ አያስፈልገውም ነበር፡ ሰውንም በደም ማዳን አያስፈልገውም ነበር። ወንጌልን በሰው በኩል መሰበክ አያስፈለገውም ነበር፥ ፀሐይ ወይም ጨረቃ ወይም ከዋክብት ወንጌልን እንዲሰብኩ ሊያደርግ ይችል ነበር፡ ነፋሳትም ወንጌልን እንዲያንሾካሹኩ ሊያደርግ ይችል ነበር። ዳሩ ግን እርሱ ሰውን መረጠ! ቃሉም የሚመጣበትን መንገድ መረጠ፡ ያም የእግዚአብሔር ቃል አካል በመሆን፡ የቃሉን መገለጥ ለዚያ ዘመንና ለዚያ ጊዜ እንዲያውጁ፡ አስቀድመው በተወሰኑትና አስቀድመው በተሾሙት በነቢያቱ በኩል ነበር። “የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነቢያት ብቻ ይመጣልና።” ወደ ሰነ መለኮት ምሁር ፈጽሞ አይመጣም። እስቲ አንድ ጥቅስ አሳዩኝ። ወደ ነቢያት ብቻ ይመጣል። እግዚአብሔር ሊዋሽ አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው በመረጠው ዘዴ፡ እንዲሁም ራሱ በመረጣቸው ነቢያቱ በኩል ነው፥ ሰው በመረጣቸው ነቢያት ሳይሆን፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በመረጣቸው ነቢያት ነው።

50 ከዚያም አማኞቹ ነቢያቸው የተናገሩት ነገር ሲፈጸም ይጠባበቃሉ፡ ያም የእግዚአብሔር ነቢያት ተብለው የሚቆጠሩበት ማረጋገጫ ነው። ምክንያቱም፡ በመጀመሪያ፡ በመንፈስ የተነዱ ናቸው። ቀጥሎም፡ ለዚያ ዘመን ከተሰጠው ቃል ጋር በትክክል ይቆማሉ። እንግዲህ ያ ማስረጃው ነው። አያችሁ፡ ባለፈው እሑድ በዚያ ላይ ተነጋግረንበታል። ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉ። በለዓምና ሙሴ ሁለቱም በአንድ መንፈስ ተቀብተው እንደነበር፡ በምሳሌ አሳይተናል፡ ከእነርሱም አንዱ፡ “እኛ ሁላችን አንድ ነን። ኑ እንቀላቀል፡ ልጃገረዶቻችንንና ሁሉንም አንድ ላይ እናድርግ። እዚህ ቆንጆ ልጃገረዶች አሉን፡ እናንተ ልጆች

ወደዚህ መጥታችሁ ለእናንተ የምትሆን ቆንጆ ሚስት ውሰዱ። ምንም ችግር የለውም፡ ያም ሆነ ይህ፡ እኛ ሁላችን አንድ ሕዝብ፡ አንድ ዘር ነን” አለ። እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ፈጽሞ ይቅር አላላቸውም። እነርሱ ያንን አዳመጡ።

51 እያችሁ፡ ዓለምና ሕ—ሕዝቡ የሆነች አነስተኛ መውጫ፡ የሆነች አነስተኛ ማለፊያ፡ የሆነች አነስተኛ አቋራጭ መንገድ ይጠባበቃሉ፡ ሆኖም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አቋራጭ መንገዶች የሉም። ያለው አንድ ንድፍ ብቻ ነው። ራስህን ከዚያ ንድፍ ጋር እንዲስማማ አድርገህ መቁረጥ አለብህ እንጂ፡ ንድፉን ለአንተ እንዲስማማ አድርገህ ለመቁረጥ መሞከር የለብህም። እያንዳንዱ ሰው ይህን ማድረግ አለበት። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርግበት ብቸኛ መንገድ ይኸው ነው።

52 አሁን አስተውሉ፡ አማኞች ያ ቃል እስኪጸና ይጠባበቃሉ። እያችሁ፡ የተጻፈው በሰው ሳይሆን፡ በጌታ አምላክ ነው፡ ስለዚህ የሰው መጽሐፍ አይደለም።

53 አንድ ሰው፡ “እነዚህ እንዲሁ ያረጁ የዕብራውያን ጽሑፎች ናቸው” አለ። ዕብራውያን ራሳቸውን የሚኮንን ደብዳቤ ይጽፉሉን? ያቺ ራሷን-ያሳመረችና የተዋበች፡ ግሩም የአይሁድ ብሔር፡ የገዛ ራሷን እየኮነነች፡ የራሷን በደሎች ትጽፍ ነበርን? ፈጽሞ አያደርጉትም። የገዛ ኃጢአቱን፡ እንዴት ወደ ጣዖት አምልኮ እንደ ገቡ፡ እንዴት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ዝሙት እንደ ፈጸሙ ይናገራልን? አይ፡ አይ። ያ ኩሩ ሕዝብ፡ ያንን ፈጽሞ አይናገርም ነበር።

54 የሰው መጽሐፍ አይደለም። የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው። ራእዮችን የሚያይ ወይም የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚሰሙት ሰዎች እንኳ፡ (ብዙ ጊዜ) ራሳቸው፡ በብዙ አጋጣሚዎች ፈጽሞ አልተረዱትም ነበር። እያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ሰው አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እግዚአብሔር ነው። ይህ አይደለም... የሰው መጽሐፍ አይደለም። የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው። በሰው ከንፈሮች በኩል የተገለጹ የእግዚአብሔር አሳቦች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያደርገውም ይኸው ነው። የተገለጸ አሳብ ቃል ነው። በመጀመሪያም የእግዚአብሔር አሳብ ነበረ፡ እርሱም በነቢያቱ ከንፈሮች በኩል ገለጸው በአገልጋዮቹም አጸናው። እያችሁ? አስተውሉ።

55 እግዚአብሔር የራሱን ምርጫ ራሱ ያደርጋል፡ አስቀድሞ በመወሰን፡ ለእያንዳንዱ ዘመን ነቢያትን መረጠ። አስተውሉት። የዚያን ነቢይ ባሕርይ ለዚያ ዘመን እንዲመጥን አድርጎ ያዘጋጀዋል። እያችሁ፡ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር፡ የእርሱን አሠራር ያመቻችለታል። የተማረም ሆነ ያልተማረ እንዲመጥን አድርጎ ያዘጋጀዋል። ስጦታዎቹን፡ የሚሰብክበትን መንገድ፡ የሚኖሩትን ስጦታዎች ያዘጋጅለታል። ለዚያ ለተወሰነው ዘመንም ያለውን መልእክት፡ እግዚአብሔር ያ የተወሰነ ነገር እንዲሆን አስቀድሞ ወስኗል የእርሱንም ስፍራ ሊወስድ የሚችል ሌላ ምንም ነገር የለም። ምንም ቢሆን ምንም፡ ምን ያህል የሰው-ሰራሽ ስኬቶች ቢኖሩም፡ ምንም ነገር ስፍራውን ሊወስድ አይችልም። ምናልባትም ያልተማረን ሰው፡ አስቀድሞ ወስኖ ይሆናል። ሌላ ዓይነት ሰው እንዲሆን አስቀድሞ ወስኖት ሊሆን ይችላል። እርሱ ምንነቱ ምንም ቢሆን፡ እርሱ ደረጃውን ይሰጠዋል፡ ስ—ስጦታውን፡ ተፈጥሮውን፡

አካሄዱን ይሰጠዋል፡ ምንም ቢሆን፡ ራሱን እንዴት እንደሚገልጽ፡ እንዲሁም የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ይሰጠዋል። የዘመኑን ሕዝብ እንዲይዝ የዘመኑን ሰው ያዘጋጀዋል። ልክ ነው። ይህን ያደርገዋል።

56 በእያንዳንዱ ዘመን መጨረሻ፡ ቤተ ክርስቲያን ወደ ዓለምና ኃጢአት ዘወር ስትል፡ እንዲሁም በሰው የቃል ትርጓሜ ላይ ስትደገፍ። እንደ ሁልጊዜው፡ እንደተለመደው፡ በዘመኑ መጨረሻ፡ በሰነ መለኮት ምሁራኖቻቸውና በካህናቶቻቸው አማካኝነት ሁልጊዜም ብጥብጥ ውስጥ ስለሚገቡ ሁልጊዜም የተመሰቃቀለ-ይሆናል። ትርጓሜያቸው ሁልጊዜም ስህተት ነው፡ አንዴም እንኳ ስህተት ከመሆን ድኖ አያውቅም። የእግዚአብሔርም ቃል አንዴም እንኳ ትክክል ከመሆን ጎድሎ አያውቅም። ልዩነቱ ይኸው ነው።

57 አሁን እያችሁ፡ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ራሱ ነው። አሁን፡ እግዚአብሔር መናገር ይችላል። ሙሴ እርሱ ተናገረኝ አለ። ኤርምያስ፡ "ቃሉን በአፌ ውስጥ አኖረ" ብሏል። እግዚአብሔርም መጻፍ ይችላል። አሥርቱን ትእዛዛት በገዛ ጣቱ ጽፏል። በባቢሎን ግድግዳዎች ላይ ጽፏል። አስታውሱም፡ በብሉይ ኪዳን ብቻ፡ ነቢያት ሁለት ሺህ ጊዜ፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**" ብለዋል! እግዚአብሔር መናገር ይችላል፡ እግዚአብሔር መጻፍ ይችላል። እርግጥ ነው። የማቴዎስ፡ የማርቆስ፡ የሉቃስና፡ የዮሐንስ፡ ዘጠና በመቶ የሚጠጋው፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ትክክለኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር መጻፍ ከቻለ፡ እግዚአብሔር ማንበብ ከቻለ፡ እግዚአብሔር መናገር ከቻለ፡ ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሊያደርግ አይችልምን? ለሙሴ፡ "ሰውን ዲዳ የሚያደርገው ወይም መናገርን የሚሰጠው ማነው" አላለውምን? እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው በነቢያት በኩል ነው፡ ይህም የእርሱ አሠራር ነው።

58 አሁን ቤተክርስቲያን በተመሰቃቀለች ቁጥር (እግዚአብሔርም ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ያውቅ ነበር፡ እርሱ ሁሉን ነገር አስቀድሞ ያውቃልና)፡ ስለዚህም ተስፋ በሰጠው መሠረት፡ በምልክቶችና በድንቆች በጸናው ቃሉ እንዲሁም ቃሉን በማረጋገጥ የተመረጡትን ለመጥራት፡ ለዚያ ዘመን የተዘጋጀ፡ "ቃሉን በሚከተሉት ምልክቶች ለማጽናት፡" የሆነ ነቢይ አለው። ነቢዩ ራሱ ከጸና በኋላ እውነተኛውን ትርጓሜ ይሰጣል።

59 እርሱ ከተላከላቸው፡ ከተመረጡት በቀር፡ ሁሉም ይጠሉታል። አሁን፡ እያንዳንዱን አጋጣሚ መርምሩና ይህ ትክክል መሆን አለመሆኑን ተመልከቱ። እርሱ ለተላከላቸው ብቻ ነው! "ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፡ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣንን ሰጣቸው።" አስተውሉ፡ ምንም... እኔ ብዙ ጊዜ እንደ ሰበክሁት፡ በቃሉ ምርምር ሁሉ፡ በእያንዳንዱ አጋጣሚ፡ እንዲሁም በእያንዳንዱ ዘመን መጨረሻ ወይም ጫፍ ወይም መገጣጠሚያ ላይ እንዲሁ ነው።

60 ከፍርዱ በፊት በነበረው ጫፍ ላይ፡ የኖኅን ዘመን ተመልከቱ። ምን ሆነ? ኖኅ፡ ያንን ሰው ያመኑት የገዛ ቤተሰቦቹ ብቻ ነበሩ። የተቀሩት ተቹት። መላውን ዓለምም አጠፋው።

61 በአብርሃም ዘመን ያመኑት፡ የአብርሃም ወገኖች ብቻ ነበሩ። መላእክቱም ሄደው ለሰዶም በሰበኩ ጊዜ፡ ሎጥና ሚስቱ እንዲሁም ሁለት ሴቶች ልጆቹ

ብቻ ወጡ፡ እርሷም ወደ ኋላ ዘወር ብላ የጨው ሐውልት ሆነች።

62 በሙሴ ዘመን፡ ከእስራኤል የተመረጡት ብቻ ወጡ። ፈርዖንም ጠላው።

63 በኤልያስ ዘመን፡ ከሰባት ሺህ ሰዎች በቀር ሌላው ሁሉ (ማለት ይቻላል)፡ እያንዳንዱ ሰው ጠልቶት ነበር፡ መላው ሕዝብ ጭምር።

64 በኤርምያስ ዘመን፡ እንዲያውም፡ ያልበሰለ ፍሬ ወረወሩበት፡ ለብዙ ቀናት በአንድ ጎኑና፡ በሌላኛው ጎኑ ሰለ ተኛ፡ እ—እንዲሁም ነገሮችን በመውሰድ ምሳሌዎችን ስላደረገ፡ አክራሪ ብለው ጠሩት። ጠሉት።

65 ነቢዩ ኢሳይያስ፡ ያንን ዘር እጅግ አድርጎ ሰለ ኮነነው በመጋዝ ለሁለት ሰነጠቁት። በትክክል።

66 መጥምቁ ዮሐንስ። "እዚያ ታች የነበረ የዱር ሰው ነው፡ የሆነ የሚጮኽ ዕብድ ነው።"

ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ቤተክርስቲያን አድርጎ ካቀረባቸው ከ—ከእነዚያ ደቀ መዛሙርት በስተቀር ሌላው ሁሉ! ይሄውና እያችሁ። ዮሐንስ ሕዝብን አዘጋጀ። ስንት ነበሩት? በሁለቱም ጣቶች... በሁለቱም እጆች፡ እርሱ ሲመጣ ዮሐንስ ለኢየሱስ ያቀረባቸው ስንት እንደሆኑ፡ በጣቶቻችሁ ልትቆጥሯቸው ትችላላችሁ። አሁን፡ ሰለ ሁለተኛው መምጣቱስ ምን ማለት ይቻላል? እስቲ አሰቡት።

67 ነገር ግን እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ቃሉ ለዘመኑ በግልጽ የጸና ሆኖ ሲያዩት፡ ያምናሉ። ከእርሱ ሊያስቀራቸው የሚችል ምንም መንገድ የለም፡ ያምኑታል። ምስክርነታቸውን በደማቸው ጭምር ያትማሉ። ያምኑታል። ያኔም ለዚያ ለተወሰነው ዘመን አስቀድመው ለተወሰኑት፡ ለሚያዩትና ለሚያምኑት ለእነርሱ ይሆናል።

68 ሌሎች ግን ሊያዩት አይችሉም፥ ታውረዋል። አሁን፡ "ሊያዩት አይችሉም፡" ትላላችሁ። አሁን፡ እንደ በለዓም፡ በለዓም ያንን ለምን ማየት አቃተው? እርሱ ነቢይ ነበር፡ የተቀባ። ፈርዖንስ ለምን ሊያየው አቃተው? የእግዚአብሔር እጅ ወርዶ በዚያ ተአምራትን ሲያደርግ ሲያይ፡ ልቡን አደነደነው እንጂ ሌላ አላደረገም። ልክ ነውን? ራሱ አይሁዳዊ የሆነው፡ ዳታንስ ለምን ማየት አቃተው? ልክ እዚያው፡ በሙት ባሕር አቋርጦ መጥቶ፡ በየሌሊቱ ትኩስ ሆኖ የሚወርደውን፡ መና እየበላ፡ አሁንም ሊያየው አቃተው። ቆሬስ ለምን አላየውም? ቀያፋስ ለምን አላየውም? እርሱ በዚያን ጊዜ የዓለም ዋነኛ የሐይማኖት መሪ ነበር። መሢሑ እንደ ሆነ ለምን አላየውም? ይሁዳስ ለምን አላየውም? ይሁዳ ልክ ከእነርሱ ጋር ነበር፡ ከእነርሱ ጋር ይራመድ ነበር፡ ከእነርሱ ጋር ተአምራትን ያደርግ ነበር። ዳሩ ግን ቃሉ መፈጸም ነበረበት። መጽሐፍ ቅዱስ እነርሱ ያንን ሰፍራ እንዲወሰዱ እንደ ተነሱ ይናገራል። የተነሱትም ለዚያው ዓላማ ነበር። ያ እውነት ነው። ሮሜ 8 ያንን ይናገራል።

69 አሁን አማኞች በትውልዳቸው ውስጥ ቃሉ ሥጋ ሲሆን፡ እግዚአብሔር ሲናገር ማየት ይችላሉ። አሁን፡ እነዚያ ትክክለኛ እውነተኛ አማኞች፡ በኤልያስ ዘመን የነበሩት እነዚያ ሰባት ሺህ (ወይስ ሰባት መቶ ነበሩ? )። ሰባት ሺህ ልክ ነው። በኤልያስ ዘመን፡ ከሁለት ወይም ሦስት ሚሊዮን ከሚጠጉት ውስጥ፡ ያ ትክክል እንደ ሆነ ያዩ ሰባት ሺህ ሰዎች ነበሩ። ከሕዝቡ አንድ መቶኛ እንኳ፡

አይሆኑም። ዳሩ ግን ትክክል እንደ ሆነ አዩ። እግዚአብሔር ሲገለጥ አዩ። ኤልሳዕ የተላከላት ያች አሮጊት መበለት፡ እንጨቶችን ለመሰብሰብ፡ ቂጣ ለመጋገር ሄደች፡ ለእርሷና ለልጅዋ የሚሆን ቂጣ ለመጋገር ብቻ የሚበቃ ነበራት፡ ከዚያም ሊሞቱ ነበር። ነገር ግን ኤልያስን ተመልከቱ፡ እንዲህ አላት፡ “አስቀድመሽ፡ ለእኔ አንዱን ጋግሪልኝ። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ጌታ አምላክ በምድር ላይ፡ ዝናብን እስከሚልክበት ቀን ድረስ ዱቄቱ ከማድጋው አያልቅም ዘይቱም ከማሰሮው አይጎድልም” አላት። ምንም ጥያቄ አላነሳችም፡ ቂጣውን ጋግራ ልትሰጠው ወዲያውኑ ሄደች። “አስቀድመሽ የኔን ጋግሪ፡ ከዚያም ሄደሽ ለአንቺና ለልጅሽ ጋግሪ፡” አላት። ያንን ሰው፡ ሰምታዋለችና፡ ተመልክታዋለችም፡ አስቀድማ የተወሰነች ዘር ነበረች።

70 ብዙዎቹ፡ “ያ ያረጀ ጨቅጫቃ እንደገና መጥቷል። በእርሱ ምክንያት እግዚአብሔር ረግሞናል” ይሉ ነበር፡ አስታውሱ፡ ኤልያስን ነው። “እስራኤልን የምታውከው አንተ ነህ፡” አለው።

71 እርሱም፡ “እስራኤልን የምታውከው አንተ ነህ” አለው። እግዚአብሔር ማንን... የማንን ቃል እያጸና እንደ ነበረ አያችሁን? የገዛ ቃሉን።

72 አሁን መጽሐፍ ቅዱስ እነርሱ የተነሱት ለዚህ ዓላማ እንደ ሆነ ይናገራል፡ ዳሩ ግን... የ—የማያምኑት። አሁን ግን እውነተኛው አማኝ የዚያ ዘመን ቃል ሥጋ ሲሆን፡ እግዚአብሔር በሰው ከንፈሮች በኩል ሲናገርና ከዚያም አደርገዋለሁ ያለውን በትክክል ሲያደርግ ማየት ሲችል፡ ያኔ ጉዳዩ እልባት ያገኛል!

73 አሁን የተቀረውን ተመልከቱ። ምልክቶችን አትመልከቱ። ምልክቶችን የምትመለከቱ ከሆነ፡ እንደ ዓለም በእርግጥ ትታለላላችሁ። ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉ ቢቻልስ የተመረጡትን እንኳ የሚያስቱ ምልክቶችንና ድንቆችን ያሳያሉ። ቃሉን ተመልከቱ። እነዚህን ካህናት፡ እነዚህን ነቢያት፡ እዚያ የቆመውን ዕብራዊ ነቢይ ተመልከቱ። ሴዴቅያስ ሁለት ታላላቅ ቀንዶችን ይዞ፡ “እኔ ከእግዚአብሔር-የተሾምኩ-ነቢይ ነኝ፡” እያለ ነበር። እውነት ነው። “እዚህ አብረውኝ ሦስት መቶ ዘጠና-ዘጠኝ አሉኝ፡ መንፈስ ቅዱስም በላያችን ሆኖ፡ ያች ምድር የእኛ እንደሆነች እያጸናና እየተናገረ ነው። እንውጣና እንውረሳት። እክዓብ ሆይ፡ በእነዚህም ቀንዶች፡ ጠላትን ከምድራችን ታስወጣለህ፡ እግዚአብሔር ምድሪቱን ሰጥቶናልና።”

74 ያንን የሐይማኖት ሰው፡ መልካሙ ሰው፡ ኢዮሣፍጥን ተመልከቱ፡ “ሌላ አንድ ተጨማሪ የላችሁምን፡” አለ?

75 “አንድ ተጨማሪ? በአንድ ሀሳብ የሚስማሙ አራት መቶ አሉ!” እርሱም፡ “አዎን፡ እዚህ አካባቢ ሌላ አንድ ተጨማሪ አለ፡ ዳሩ ግን እጠላዋለሁ” አለው። “ሁልጊዜ ሁላችንንም ይወቅሰናል ምን ያህል ታላላቅ ኃጢአተኞች እንደ ሆንንና፡ ሌላውንም ነገር ሁሉ ይነግረናል፡” አለ። እናም፡ “እጠላዋለሁ! እርሱም፡ የይምላ ልጅ፡ ሚክያስ ነው” አለው።

76 እርሱም፡ “ኦህ፡ ንጉሡ እንዲህ አይበል። ሄዳችሁ አምጡትና ምን እንደሚል እንስማ” አለው።

77 ስለዚህ ወደዚያ አመጡት። እርሱም፡ “የዛሬዋን ሌሊት ስጡኝና ጌታ ስለ ጉዳዩ የሚለውን ልይ” አለ።

78 አክዓብም፡ “እውነትን እንጂ ሌላ እንዳችም ነገር እንዳትነግረኝ፡ አምልሃለሁ” አለው።

79 ያም ሰው መጥቶ፡ “አሁን፡ ዳግመኛ ጥሩ ኅብረት እንዲኖርህ ከፈለግህ፡ ልክ እንደ ሌሎቹ ተናገር፡” አለው።

ሚክያስም፡ “እግዚአብሔር የሚለውን ብቻ እናገራለሁ” አለ። አያችሁ?

80 በማግስቱ ጧት፡ ወደ ውጭ ወጡ። ነገሥታቱ ልብሶቻቸውን ለብሰው፡ ታላላቆቹም ሁሉ፡ በበሩ አጠገብ ተቀመጡ። ነቢዩም እዚያ ቆሞ ነበር። “አሁን፡ አንተ አክራሪ፡ ስለ ጉዳዩ ምን ትላለህ፡” አለው?

81 እርሱም፡ “ውጣ” አለው። ቀጥሎም፡ “ነገር ግን እስራኤል እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተበትነው አየሁ” አለው።

82 እርሱም መታ-... እጁን አንስቶ አፉን መታው። ነቢዩ ነቢዩን አፉን መታው። አሁን፡ እነዚያ የተቀቡ ነቢያት ሁለቱም እዚያ ቆመው፡ አራት መቶ በአንድ ላይ ሆነው፡ ትንቢት ተናገሩ፡ ያም በጣም ጠንካራ ይመስል ነበር። አሁን፡ ሁልጊዜም ደህንነት በምክር ብዛት አይገኝም። የሚወሰነውም የት... ስለ ምን እንደሚመካከሩና፡ ምክራቸው ምን እንደ ሆነ ነው። ለንጉሡ በዚያ ደህንነት አልነበረም፡ እርሱ ግን ያንን ብዙ ሕዝብ ምክራቸው ትክክል እንደ ሆነ አድርጎ ወሰደው። ነገር ግን ጥቂት ቆም ብሎ የብራናውን ጥቅልል ወደ ኋላ መልሶ ኤልያስ ምን ብሎ እንደ ተናገረ ቢመለከት ኖሮ!

83 ያኔ፡ ምናልባት እግዚአብሔር ለዚያ ነገር ይቅር ብሎት እንደ ሆነ፡ ስለማያውቅ፡ ሚክያስ እንዳችም ነገር መናገር አልቻለም። ነገር ግን አስቀድሞ፡ ነቢይ እንደ መሆኑ መጠን፡ እግዚአብሔር ምን እንዳለ ለማወቅ ወደ እግዚአብሔር ሄደ። እግዚአብሔር ያለውንም አወቀ። እርሱም እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር በዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁ፡ እርሱም... የሰማይ አማካሪዎቹን ሁሉ በዙሪያው ሰብስቦ፡ እንዲህ አለ፡ ‘ስለ እርሱ የተነገረውን ትንቢት በተግባር እንድንፈጽም፡ ወርዶ አክዓብን ወደዚህ እንዲመጣ የሚያደርግልን ማንን እናገኛለን? ’”

84 አያችሁ፡ ትንቢት፡ ኤልያስ ቀድሞውንም፡ “ውሾች ደምህን ይልሳሉ” ብሎ ተናግሮ ነበር።

85 ስለዚህም “አንድ ሐሰተኛ መንፈስ ከታች ሲወጣ፡ ወጥቶም፡ በእርሱ ፊት ቀርቦ፡ ‘እኔ ወርጄ በነቢያቱ፡ በአክዓብ ነቢያት ውስጥ እገባለሁ፡ ሐሰትንም ትንቢት እንዲናገሩ አደርጋቸዋለሁ’ ሲል አየሁ፡” አለ።

86 አሁን፡ እግዚአብሔር እነዚያ ሰዎች እጅግ ታብየውና በሰነ መለኮት ተሞልተው ሁሉንም ነገር በትክክል እንደያዙ ያሰቡ እንደነበር ያውቅ ነበር። ለዘመኑ የተሰጠውን ቃል ፈጽሞ አላስተዋሉም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር፡ “ይሳካልሃል፡ ውረድ” አለው። ሚክያስም ያንን ሲናገር፡ በክፉ መንፈስ ስር ሆነው ትንቢት እየተናገሩ መሆናቸውን አረጋገጠ። የስልኩን መስኪያ በነቀሉ፡ ወይም ሬዲዮውን ባጠፉ፡ ወይም ማንኛውንም ነገር ባደረጉ ነበር፥ ይህ በእነርሱ ላይ ሲመጣ ሲሰሙ፡ ተነስተው ወጡ። ነገር ግን ምን እንደ ሆነ ተመልከቱ። አሁን፡ ሚክያስ ራእዩን ከተጻፈው ቃል ጋር ማረጋገጥ ነበረበት፡ ስለዚህም ያውቅ ነበር።

87 እርሱም፡ “ሰመጣ... ያንን ሰው በወኅኒ አኑሩት፡ የመከራንም ውኃና የመከራን እንጀራ ሰጡት። ሰመለስ፡ አገኘዋለሁ” አለ።

88 እርሱም፡ “ከተመለስክ፡ እግዚአብሔር አልተናገረኝም” አለው። ያኔም ራእዩ ለዚያች ሰዓት ከተሰጠው ቃል ሁሉ ጋር በትክክል አንድ እንደሆነ አወቀ። ያ የአክዓብ ጊዜ ነበር።

89 ወንድሜ፡ እኅቴ፡ ይህ ከባቢሎን የምንጠራበት ዘመንና ጊዜ ነው። የምሽት ብርሃናት እዚህ አሉ። ብርሃን ሳለ በብርሃን ተመላለሱ። አስተውሉ፡ አማኞች ቃሉ ሲገለጥ አዩ አመኑትም። ኢየሱስ፡ “በጎቼ ድምፄን፡ ቃሌን፡ የዘመኑን ምልክቶቼን ያውቃሉ። ሐስተኛውንም አይከተሉም” አለ።

90 አሁን ወደ ርዕሳችን እንግባ፡ ምክንያቱም እየራቅሁ እንደሆነ አይቻለሁና። በዚያ የጸሎት መሰመር ላይ አጥብቄ ትኩረት ማድረግ እፈልጋለሁ። አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች፡ እያሰብንበት ወዳለው ክፍላችን እንመለስ። መልካም፡ እንደ ተለመደው፡ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ዳግመኛም ይሆናል።

91 እግዚአብሔር ቃሉ እንደ ተናገረው፡ ነቢዩን፡ ዮሐንስን፡ በሚልክያስ 3 ላይ፡ “እነሆ፡ መንገድን እንዲያዘጋጅ፡ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ” ተብሎ በተገባው የተሰፋ ቃል መሠረት ላከው። ዮሐንስም ለዚህው ነገር መሰከረ። እንዲሁም፡ በኢሳይያስ 40፥3 ላይ፡ ኢሳይያስ፡ “በምድረ በዳ፡ ‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ’ ብሎ የሚጮኽ የነቢይ ድምፀ ይሆናል፡” እንዳለ እናገኛለን። አያችሁ? እነዚያ ትንቢቶች ሁሉ! እ—እንዲሁም ተመልከቱ፡ ቶሎ ብላችሁ አስተውሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ገልጧል።

“አንተ ማን ነህ? መሢሑ ነህን፡” ባሉት ጊዜ?

እርሱም፡ “አይደለሁም” አለ።

“ኤርምያስ ነህን? ነቢያት፡ ወይስ ከእነርሱ አንዱ ነህን? ”

92 እርሱም፡ “አይደለሁም። ዳሩ ግን ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ፡ እኔ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፀ ነኝ” አለ።

93 ያንን የሚያምኑ ይመስላችኋልን? በጭራሽ፡ አላመኑም። ለምን? የመጣው በቤተ ክርስቲያናቸው በኩል አልነበረም። ከእነርሱ... አያችሁ፡ በዘጠኝ ዓመት ዕድሜው ወደ ምድረ በዳ ገብቶ፡ በሠላሳ ዓመቱ ወጣ። መልእክቱ በሰነ መለኮት ትምህርት ቤት ውስጥ ሊያልፍ የማይችል እጅግ ታላቅ ነበር፡ እርሱ መ—መሢሑን የሚያስተዋውቅ ሰው ነበርና። እያንዳንዱ ሰው **ወደዚህና ወደዚያ** ይጎትተው ነበር። እግዚአብሔርም አባቱ ዘካርያስ፡ ከሞተ በኋላ፡ ወደ ምድረ በዳ ላከው። እርሱም ካህን ነበር፡ ዳሩ ግን የአባቱን መሰመር ፈጽሞ አልተከተለም።

94 ምክንያቱም፡ ነቢያት ከእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ውስጥ አይወጡምና። እነርሱ ከሻካራው ምድር፡ ከምድረ በዳ ይመጣሉ። ከየት እንደመጡ፡ ወይም ወደ መድረኩ እንዴት ብቅ እንደሚሉ፡ ወይም ታሪካቸው ምን እንደሆነ የሚያውቅ ማንም የለም። እነርሱ እንዲሁ ብቅ ይሉና ቃሉን ይሰብካሉ፡ እግዚአብሔርም ይወስዳቸዋል፡ እነርሱም ይሄዳሉ፥ ያንን ትውልድ ይኮንናሉ፡ ደግሞም ታላቁን ቀን እየተጠባበቁ፡ ወደ ቃሉ ውስጥ ዘልቀው ይገባሉ።

95 ቤተ ክርስቲያንም አላመነችውም፡ ምክንያቱም በእነርሱ ዘንድ የሚታወቅ አልነበረምና። በመጻሕፍቶቻቸው ውስጥ የክህነት ሹመቱ የተመዘገበበት ምንም ማረጋገጫ አልነበራቸውም፡ ስለዚህም አልተቀበሉትም። እያችሁ፡ ያንን የጸናውን የእግዚአብሔርን ቃል፡ በግልጽ፡ ፊደል በፊደል አላመኑም። እያችሁ? ሚልክያስ 3፡ እርሱን የሚያጸኑ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ነበሩ፡ ሚልክያስ 3ና ኢሳይያስ 40፥3። እያችሁ፡ ሁለቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፡ የጌታን መንገድ እያዘጋጀ ስለሚመጣው ሰው ይናገራሉ። እርሱም የተባለውን መስፈርት ሁሉ አሟልቷል።

96 እርሱ ነቢይ መሆን ነበረበት። “ኤልሳዕን እልክላችኋለሁ።” ልክ እንደ ተባለውም፡ እርሱ በዚያ ሻካራ በሆነው መንገድ ሁሉ እዚያው ነበረ። ባሕርዩ ከኤልያስ ጋር እንዴት እንደተዋሃደ ተመልከቱ። ኤልያስ የምድረ በዳ ሰው ነበረ፡ ዮሐንስም እንዲሁ ነበረ፥ የውጭ ሰው። እርሱ የለዘበ ሰው አልነበረም፡ እርሱ ሻካራ ሰው ነበረ።

97 እንደገና አስተውሉ፡ ኤልያስ ሴቶችን የሚጠላ ሰው ነበረ፡ ኤልዛቤል ስለተቀባችው ቀለም ሁሉ፡ እንዲሁም የት መቆም እንዳለባት ነግሯት ነበር። ዮሐንስም እንዲሁ ነበረ። ኤልዛቤል ኤልያስን ለመግደል ሞከረች፡ ራሱንም እንደምትቆርጥ በአማልክቷ ምላለች። ሄሮድያዳም እንዲሁ አድርጋለች። እያችሁ?

98 ሁልጊዜም መልእክታቸውን ተመልከቱ፡ ያደረጉትንም ነገር ተመልከቱ። አሁን እነርሱ ወደ ኋላ ተመልሰው መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቢያዩ ኖሮ፡ የሰውየውንም ባሕርይ እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስና ከነገሮች ሁሉ ጋር በወቅቱ ምን ያህል ፍጹም እንደነበረ ቢመለከቱ ኖሮ፡ ያ እርሱ እንደነበረ ማወቅ እንደነበረባቸው እናገኛለን። የተወሰኑት ብቻ አውቀውት ነበር። በትክክል። የተወሰኑት ብቻ ተገንዝበውት ነበር። እርሱን ለመስማት ሄዱ፡ ዳሩ ግን አላመኑበትም ነበር። እያችሁ? ለምን? በዘመናቸው የነበረውን የትንቢት መፈጸም አላመኑም ነበርና።

99 አስተውሉ፡ በእርሱ ላይ ሳቁበት፡ “የሚጮኽ፡ የዱር፡ ትምህርት ቤት ያልገባና ያልተማረ አክራሪ፡ ‘ሂት፡ ሄይንት፡ ቶት፡ ካሪ፡ ፌች’ የሚልና የመሳሰሉትን፡” በማለት ጠሩት። እንደተለመደው በትምህርቱ መዘኑት። በሰዋሰው አጠቃቀሙ፡ በአለባበሰ ሁኔታው መዘኑት። የበግ ቆዳ በዙሪያው አድርጎ፡ የግመል ቆዳ ቀበቶም ታጥቆ ነበረ፡ እርሱ ሙሉ በሙሉ ጠጉራም ነበረ። በውኃዎች ውስጥ ይራመድ ነበረ፥ ቤተ ክርስቲያን የለው፡ የወንበር መቀመጫ የለው፡ ትብብር-አልባ፥ ያንን ሊቀበሉት አልቻሉም፥ የዓለምን አምላክ ያመልኩ ነበርና። እያችሁ?

100 አሁን እንደ ኢያንበሬስና ኢያኔስ ያሉ፡ ሐሰተኛ ነቢያት አይነሱም ማለቴ አይደለም። ዳሩ ግን ልታደርጉት የሚገባው መንገድ፡ የመጀመሪያውን መልእክት በቃሉ መመርመር ነው፡ ያኔ ታገኙታላችሁ፥ በየትኛው ዘመን ውስጥ እንዳለ፡ ለዚያ ዘመንም ምን ትንቢት እንደተነገረ ማየት ነው።

101 ከዚያም የዮሐንስ ትንቢት በእግዚአብሔር በራሱ ሥርዓት ጸና። ምን ያህል ፍጹም እንደ ሆነ ተመልከቱ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “የጌታ ቃል ወደ ነቢይ ይመጣል” ይላል። ኢየሱስም ቃል ነበረ። ዮሐንስም ቃሉ ሊፈጸም ስለ መምጣቱ ትንቢት

ይናገር ነበር፥ ቃል የሆነው፡ ኢየሱስም፡ በውኃው ውስጥ፡ ወደ ነቢዩ መጣ። ኦህ፡ ምንኛ ያማረ ነው! ምን ያህል የማይወድቅ ነው... አያችሁ? በዚያ ዘመን ቃሉ እጅግ ብርቅ ነገር ነበረ። እነሆ ነቢዩ፡ “እኔ የቃሉ ድምፀ ነኝ፡” እያለ መጣ።

እነርሱም፡ “ምን ማድረግ አለብን” አሉ?

102 እርሱም፡ “የጫማውን ጠፍር ልፈታ እንኳ አልበቃም። ዳሩ ግን በመካከላችሁ፡ የሆነ ቦታ የቆመ አንዱ አለ፡ እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል። መንሹም በእጁ ነው፡ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፡ ገለባውን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል፥ ስንዴውን ግን ወደ ጎተራ ይሰበስባል” አላቸው። ኦህ፡ እንዴት ያለ ነቢይ ነው! እስከዚያች ቀን ድረስ፡ ከሴት ከተወለዱት መካከል እንደ እርሱ ታላቅ የሆነ ሰው ፈጽሞ እንዳልተነሳ ኢየሱስ ተናገረ። ኦህ፡ እንዴት ያለ ደፋር ነበረ! የት እንደ ቆመ እንዴት አጥብቆ ያውቅ ነበረ! በትክክል ያውቅ ነበር። ከእግዚአብሔር ሰምቶ ነበር፡ ያም ከቃሉ ጋር በትክክል አንድ ነበረ፡ ስለዚህ ሰዎች ስለሚሉት ነገር ምንም አልገደደውም። ያም ሆነ ይህ እርሱ ሰበከው፡ ትንቢትም ተናገረበት። አስተውሉም፡ አንድ ሰው እውነት ለሆነው ነገር በሚቆምበት ጊዜ፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ለዚያ ሰው እውነቱን ለማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

103 ሙሴ እዚያ ግብፅ ወርዶ፡ እንዲህ አለ፡ “ወዲያ በምድረ በዳ ሳለሁ፡ አንድ ዛፍ በእሳት ሲቃጠል አየሁ፡ ዳሩ ግን አልነደደም። ወደ ዛፉም ቀረብኩ፡ ስቀርብም፡ እዚያ ላይ የተንጠለጠለ፡ ታላቅ የእሳት ዓምድ ነበረ። አንድ ድምፅም፡ ‘**ያለሁና የምኖር እኔ ነኝ**’ አለ። ይህችንም በትር ይዤ ወደዚህ እንድወርድና እነዚህን ተአምራት እንዳደርግ ነገረኝ፡ እግዚአብሔርም ቃሉን ያጸናል” ባለ ጊዜ። በትሩን ዘረጋ፡ ቅማልና ዝንብ፡ ጨለማም ሌላውም ነገር ሁሉ መጣ። ከዚያም ያንን ነቢይ ለማጽናት፡ እነዚያን አማኞች ወደዚያው ተራራ መለሳቸው፡ እግዚአብሔርም በዚያው የእሳት ዓምድ፡ ልክ በዚያው ተራራ ላይ ወረደ፡ ያም ትክክል እንደ ነበረ አረጋገጠ።

አሁን በዚህ ዘመን ያደረገውን ተመልከቱ። በትክክል።

104 አሁን፡ ቃሉ ወደ ነቢዩ መጣ እርሱም እውነተኛው ሰው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናል ብሎ የተናገረለት ያው ትክክለኛው ሰው እንደ ሆነ አጸናው። አሁን ፈጠን ብለን። ነገር ግን፡ እንደገና፡ ኢየሱስ የመጣው እነርሱ ለትንቢቱ ከሰጡት የሰው-ሰራሽ ትርጓሜ በተለየ መልክ ነበረ። ሰው ምን ሊሆን እንደሚችል ተርጉሞት ነበረ። እርግጥ ነው። ፕሬስባይቴሪያኖች እነርሱ መሆን እንዳለባቸው ያስባሉ። እግዚአብሔር አንዳች ነገር ሲያደርግ ተመልከቱ፡ ሌሎች ድርጅቶች ሁሉ የራሳቸውን ይዘው ሲነሱ ተመልከቱ። አዎ፡ ሁልጊዜም እንደዚያ ነው። በየቦታው ኢያንበሬስና ኢያኔስ አሏቸው። አስተውሉ፡ ከቃሉ ከፊሉን ብቻ ተናገሩ። ዳሩ ግን፡ በነቢዩ ቃል መሠረት፡ እያንዳንዱ ፊደል ነው!

105 እንደ ተለመደው፡ ዳግመኛም አጡት፡ ሟርተኛ፥ “አጋንንት፡ ብዔልዜቡል” ብለው ጠሩት፡ በገዛ መጽሐፍ ቅዱሳቸው፡ እርሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፡ ማወቅ ሲገባቸው፥ ራሱን አምላክ አደረገ አሉ።

አስተውሉ፥ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮለት ነበረ፥ በኢሳይያስ 9፥6 ላይ፡ አለ፡ “ሰሙ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ይባላል” ብሏል። ከዚያ በኋላ ሌላ አባቶች ፈጽሞ አይኖሩም፡ ምክንያቱም እርሱ በመጀመሪያው ፊተኛው አባት

ነበረና፡ እርሱ ብቸኛው አባት ነው፥ ስለዚህም፡ “ከዚህ በኋላ፡ ማንንም የዚህችን ምድር ሰው ‘አባት፡’ ብላችሁ አትጥሩ፡” አለ። “ኃ—ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት፡ መካር፡ የሰላም አለቃ ነው።” እርግጥ ነው።

106 አሁን፡ ነቢያት ሁሉ ያደርጉበታል ብለው የዘረዘሩትን ሁሉ በእርሱ ላይ አድርገውበታል፡ ልክ አሁን ባለንበት በዚህ የሎዶቅያ ዘመን እንደሚያደርጉት፡ ከቤተ ክርስቲያን አወጡት። “ዕውር፡ ዕራቁቱን የሆነ፡ ይህንም የማያውቅ።” ልክ ነቢዩ እንዳለው፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ እንዳለው ነው። በሰው ትውፊት ታውረው፡ እንደ ተለመደው፡ ስለ እነርሱ ትንቢት እንደ ተነገረው፡ እርሱን አወጡት፡ ቃሉን ከቤተ ክርስቲያኖቻቸው አወጡት።

107 አሁን አስተውሉ፡ አሁን ፈጠን ብላችሁ። አሁን ይህ እንዳያመልጣችሁ። ኢየሱስ መሢሐቸው እንደ ሆነ ራሱን ለእነዚህ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት እንዴት እንዳሳወቀ፡ ጽሑፉ ይኸውላችሁ! አሁን፡ ዓይኖች ሁሉ ወደዚህ ይሁኑ። በውጭ በየሀገሩ ያላችሁም፡ አሁን ይህ እንዳያመልጣችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር በሰዎች ከንፈርና መሣሪያነት የጻፈው፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ልንነግራችሁ ሞክረናል። እግዚአብሔር ራሱ መጻፍ ይችላል። እግዚአብሔር ራሱ መናገር ይችላል። እግዚአብሔር የፈለገውን ማድረግ ይችላል፡ ነገር ግን የጻፈው ሰው የእግዚአብሔር አካል ስለሆነ፡ ያንን እንዲያደርግ ሰውን መረጠ። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ጻፈ። ሰዎቹ በገዛ ሰብዓዊ አስተሳሰባቸው፡ ምን እየጻፉ እንደ ነበረ እንኳ ኢያውቁም ነበር። ከእርሱ ጋር ላይስማሙ ይችሉ ይሆናል፡ ነገር ግን ጻፉት። ሊቃወሙት አልቻሉም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አለ፡ “የቀድሞ ሰዎች፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ሲንቀሳቀሱ!” እግዚአብሔር በራእዮች ውስጥ እጆቻቸውን አንቀሳቀሰ፡ ዓይኖቻቸውን አንቀሳቀሰ። ከሚያዩት ነገር ውጭ ሌላ አንዳችም መናገር አይችሉም ነበር። ምላስን፡ ጣትን፡ እያንዳንዱን የሰውነት ክፍል እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይመራው ስለነበር፡ አንዳችም መናገር አይችሉም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ አማልክት ናቸው ማለቱ እያስገርምም፡ እነርሱ የእግዚአብሔር አካል ነበሩና! እርሱ የእግዚአብሔር ሙላት ነበረ።

108 ቃሉ የሆነው፡ ኢየሱስ፡ ለእነዚህ ልባቸው ለተሰበረ ሁለት ደቀ መዛሙርት፡ መሢሐቸው፡ የተሰፋው ቃል የሆነው መሢሕ እርሱ እንደ ሆነ እንዴት እንዳሳወቃቸው አስተውሉ። ያደረገውን አስተውሉ፡ ወደ ትንቢት ነው የጠቆማቸው። አስተውሉ፡ “እናንተ የማታስተውሉ፡ ነቢያት የጻፉትን ሁሉ ለማመን የዘገያችሁ ናችሁ” አላቸው። አሁን፡ ፈጽሞ እንዲህ አላለም፡ “መልካም፡ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጉዳዩ፡ ምን ትላለች?”

109 እነርሱም ታሪኩን ነገሩት። የተፈጸሙትን ክንውኖች ሁሉ ያውቁ ነበር። ሁሉም አዝነው ነበር። እነርሱም እንዲህ እያሉ ይነግሩት ጀመር፡ “አንተ በዚህ እንግዳ ነህን? ወይስ በኢየሩሳሌም የሆነውን አታውቅምን?”

110 እንደማያውቅ ሆኖ፡ “ምን ነገሮች?” አለ። እያችሁ፡ ስለ ጉዳዩ ምን እንደምታደርጉ ለማየት ብቻ አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን ያደርጋል። እያችሁ? እንዲህ አላቸው፡ “ምን ነገሮች? ማነው የነበረው? ምን ተፈጠረ?”

111 “አንተ በዚህ እንግዳ ነህን?” አብረውት ለሦስት ዓመት ተኩል ከኖሩት ሰው ጋር ልክ ፊት ለፊት እየተነጋገሩ ነበር፡ ዳሩ ግን አላወቁትም ነበር።

“ምን ነገሮች? ምን ተፈጠረ? ”

112 “መልካም፡” እነርሱም እንዲህ አሉ፡ “እርሱም ነቢይ የነበረው፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። በአእምሮአችንም እንዳችም ጥርጥር የለም። በሕዝቡ ሁሉ ፊት በቃልና በሥራ ኃያል ነበረ። ለዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ነቢይ ሆኖ እስኪቆጠር ድረስ ነገሮችን ሲያደርግ አይተነዋል። ያንንም እናውቃለን። ደግሞም ቤዛ እንደሚሆን፡ እስራኤልን እንደሚቤዥ አምነን ነበር” አሉ።

113 ከዚያም ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው፡ “እናንተ ሰነፎች፡ ነቢያት ስለ እርሱ የተናገሩት ሁሉ እንደሚፈጸም ለማመን ልባችሁ የዘገየ? ” አያችሁ? አሁን ወደ ትንቢት ሲመለስ ተመልከቱት። አመንነው ለሚሉ አማኞች፡ ይህ እንዴት ያለ ተግሣጽ ነው!

114 ጉዳዩን እንዴት እንደጀመረው አስተውሉ። ቀጥታ ወጥቶ፡ “እኔ መሢሐችሁ ነኝ” ፈጽሞ አላለም። ያንን ማድረግ ይችል ነበር፡ እርሱ ነበረና። ዳሩ ግን አስተውሉ በቃሉ ውስጥ ራሱን ለየ፡ ያኔ ሊያውቁት ይችሉ ነበር። እንዲያ ብሎ ቢሆን ኖሮ፡ ያንን ሊል ይችል ነበር ሆኖም እንዲሁ ባልሆነም ነበር፥ ዳሩ ግን ሄዶ ነቢያት ሁሉ ስለ እርሱ የተናገሩትን መናገር ሲጀምር፡ እነርሱም ያንን ሲያዩ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ፡ ለራሳቸው መናገር ይችሉ ነበር። ዳሩ ግን ነቢያት አስቀድመው ወደ ተናገሩት ነገርና መሢሑ፡ በዘመኑ፡ የሚገለጥበት ጊዜ ሲደርስ ምን መጠበቅ እንዳለባቸው ወዳሉት ነገር ትኩረታቸውን ሳበ። እርሱም፡ እንደ ዮሐንስ፡ ቃሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንደ መልእክታቸው ሆኖ እንዲቆጠር አደረገ። ማንኛውም እውነተኛ ነቢይ ያንን ያደርጋል። አዎን። ዝም ብሎ ወጥቶ እንዲህ አይልም፡ “እኔው ነኝ። እኔም... ” ያ እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ አይደለም። አያችሁ? ነገር ግን፡ “ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለሱ” አለ። አያችሁ፡ እርሱ አሠራሩን ፈጽሞ አይስትም። አያችሁ?

እርሱም፡ “ሙሴን እናውቃለን” አለ።

115 እርሱም፡ “ሙሴን አውቃችሁት ቢሆን ኖሮ፡ እኔንም ባወቃችሁኝ ነበር” አለ። “ሙሴ ስለ እኔ ጽፏል፡” አላቸው። እንዲህ አለ፡ “መጽሐፍትን መርምሩ፡ በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁና፡ ስለ እኔ የሚመሰክረውም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሄዳችሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልጉና እዩት” አለ።

116 እዚህ ላይ አሠራሩን ፈጽሞ አይለውጥም፡ ለውጦም አያውቅም። ሊለውጥም ፈጽሞ አይችልም፡ ምክንያቱም እርሱ የማይለወጥ አምላክ ነውና። አያችሁ? በኤማሁስ መንገድ ላይ ቀጥታ ወደ እነዚያ ሁለት ደቀ መዛሙርት፡ ወደ ቀለዮጳና ጓደኛው፡ እንዴት እንደ ተመለሰ አስተውሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስንም ጠቅሶላቸው፡ ተናገራቸው፡ እንዲህም አለ፡ “ነቢያት ስለ መሢሑ የጻፉት እያንዳንዱ ቃል መፈጸም እንዳለበት ላለማመን ለምን እንዲህ የማታስተውሉ ሆናችሁ? ” ኦህ፡ እንዴት ያለ ቀን ነው!

117 ዮሐንስም ያደረገው ይኸው ነው። “መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ፡ ወደ ኋላ ተመልከቱ፡ ‘በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ’ እንደሚኖር ተናግሯል። ከየት መጣሁ? ” አያችሁ? ያ፡ ያ ለእነርሱ ግልጽ ሊያደርግላቸው ይገባ ነበር። በትክክል!

118 መንፈስ ቅዱስ ሲያደርግ የምናየው ነገር፡ ዛሬም ግልጽ ሊያደርግልን ይገባል። እርሱ በአንድ ወቅት፡ “መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ” ብሏል። እኛም... ዛሬ ይህን እንድናደርግ ይፈልጋል።

119 አስተውሉ፡ በሙሴ ትንቢት ጀመረ፡ መጽሐፍ ቅዱስም፡ “ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ” ይላል፡ እርሱ ግን በሙሴ ጀመረ። “ነቢይ” ሙሴም፡ “ጌታ አምላካችሁ ከሕዝባችሁ መካከል፡ ከሕዝቡ መካከል ነቢይን ያስነሳላችኋል። ጌታ አምላክ ነቢይን ያስነሳል” ብሏል።

120 አሁን ምናልባትም፡ “ቀለዮጳ፡ አንተና እዚህ ያለው ጓደኛህ፡ ጌታ አምላክ በእነዚህ ቀናት ነቢይን እንደሚያስነሳ ሙሴ አልተናገረምን? እነርሱ የሰቀሉት ይህ ሰውስ፡ ያንን መሰፈርት አሟልቷልን? አሁን፡ ሙሴ ይህንን ትንቢት ተናግሯል። እናንተም ለመቶዎችና ለመቶዎች ዓመታት ነቢይ አልነበራችሁም፡ እነሆም ይህ ሰው ተነሳ። ለመሆኑ የዚህ ሰው መንገድ ጠራጊ ማን ነበረ፡ አላችሁኝ? ” ብሎ ሊሆን ይችላል። ገባችሁን? ነቢያት ሁሉ ስለ እርሱ የነገሩትን፡ ለዘመኑ የሚሆነውን ሁሉ፡ ለእነርሱ ተናገረ። እርሱን ማዳመጥ በእርግጥም እጅግ ማራኪ ይሆን ነበር። ልትሰሙት አትወዱም ነበርን? ነቢያት ስለ እርሱ ምን እንዳሉ ሲናገር ልሰማው፡ እርሱን ልሰማው እወድ ነበር፡ ሆኖም ራሱ እንደ ሆነ ፈጽሞ አልተናገረም። በትንቢት አሳያቸው እንጂ። እርሱም፡ “ነቢዩ ይህ እንደሚሆን ተናግሯል” ብቻ አላቸው። አያችሁ?

121 ለጥቂት ደቂቃዎች ወደ ኋላ እንመለስ፡ አሁን ከእርሱ ከተጠቀሱት ቃላት እናዳምጥ። እዚህ ላይ ቃሉ ራሱ ስለ ራሱ የተነገረውን ቃል ሲጠቅስ፡ ተመልከቱ። ቃሉ ራሱ ስለ ራሱ የተነገረውን ቃል ሲጠቅስ። እርሱ ያ እንደ ሆነ አልነገራቸውም፡ ዳሩ ግን ቃሉ ስለ ራሱ እንዲናገር አደረገ፡ ያኔ እርሱ ማን እንደ ሆነ አወቁ። የቃሉ ፊደል፡ ቃሉን ሲጠቅስ በ... ሥጋ የሆነው ቃል፡ የፊደሉን ቃል ሲጠቅስ፡ ሙሉ በሙሉ ከራሱ ጋር ተቆጠረ። እዚህ ላይ ተመልከቱ፡ አሁን ሲጠቅስ እናዳምጠው። እንዴት... አሁን፡ ስለ ቅርብ ጊዜ ነገሮች ሁሉ እንደ ተነገራቸው እናውቃለን፡ ማለትም፡ ስለ ሰቅለቱና ስለ ትንሣኤው ታሪክ፡ አሁን እንዳነበብነው፡ ስለ መቃብሩ። አሁን ስለ ራሱ ወደ ተነገረው የትንቢት ቃል ቀጥታ ወደዚያ ያሳያል። አሁን ይህን እንዳለ ብቻ እናስብ፥ ከዚህም እጅግ የላቀ ተናግሯል፡ ነገር ግን ተመልከቱ።

122 እንዲህ ሲል እናስበው... እንዲህ ሲል እንሰማው፡ “ወደ ዘካርያስ 11፥12 ግለጡ። ነቢዩ እንዳለው፡ መሢሑ በሠላሳ ብር፡ ሊሸጥ አልነበረምን? እናንተም ይህ ሰው በሠላሳ ብር እንደ ተሸጠ አሁን ተናገራችሁ። ግለጡ... ” እነዚያን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እያገኛችኋቸው ነውን? ዘካርያስ 11፥12። ከዚያም እንዲህ አለ፡ “ዳዊት በመዝሙር፡ በመዝሙር 41፥9 ላይ ያለውን አስተዋላችሁን? በወዳጆቹ አሳልፎ ይሰጣል። ደግሞም እንደገና፡ በዘካርያስ 13፥7 ላይ፡ በደቀ መዛሙርቱ ይተዋል። በመዝሙር 35፥11 ላይ ደግሞ፡ በሐሰት ምስክሮች ይከሰሳል። እናንተም ልክ እንደዚያ እንደ ሆነ ተናገራችሁ። ኢሳይያስ 53፥7፡ በከሳሾቹ ፊት ዝም አለ። ኢሳይያስ 50፥6 ላይ፡ ነቢዩ እንዳለው፡ ገርፈውታል። መዝሙር 22፡ በመስቀል ላይ እንዲህ በማለት ይጮኻል፡ ‘አምላኬ፡ አምላኬ፡ ስለ ምን ተውኸኝ? ’ ከትናንት ወዲያ ከሰዓት በኋላ፡ ያንን አድርጓልን? እንደገና በመዝሙረ ዳዊት 22፡ ቁጥር 18 ላይ፡ ልብሶቹን በመካከላቸው ተከፋፈሉ። ያንን አድርገዋልን? እንዲሁም በመዝሙረ ዳዊት

22፡7 እስከ 8፡ በጠላቶቹ፡ በቤተ ክርስቲያን ተዘበተበት። ደግሞም መዝሙር 22 ላይ፡ ከአካሉ አንዱ አጥንት እንኳ አይሰበርም፡ ነገር ግን 'እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ፡'" አለ። በዚያን ጊዜ፡ ያለ ጥርጥር፡ እጆቹን ወደ ኋላው አድርጎ ነበረ። "ኢሳይያስ 53፥12 በክፉ አድራጊዎች መካከል እንደሚሞት ይናገራል። ኢሳይያስ 53፥9 ከባለጠጎች ጋር እንደ ተቀበረ ይናገራል። መዝሙር 16፥10፡ 'ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፡ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትፈቅድለትም' ይላል። ለዚህ ሰው መንገድ ጠራጊው ሚልክያስ 3 አልነበረምን? " ኦህ፡ ያንን ሲጠቅስ ብሰማው ምንኛ ደስ ባለኝ። ትንቢቶቹን ተመልከቱ! አስተውሉ፡ ከዚያም እግዚአብሔር፡ በይስሐቅ በኩል፡ አስቀድሞ እንዴት እንዳሳየ፡ በዘፍጥረት 22፡ አባባ አብርሃም የገዛ ልጁን እንዴት እንደ ወሰደ፡ እንጨቱን ተሸክሞ ወደ ተራራው ወጥቶ፡ የገዛ ልጁን መሥዋዕት አድርጎ እንዳቀረበ ስለ ይስሐቅ፡ ስላለፈባቸው ጥላዎች ሁሉ ተናግሮ ይሆናል።

123 አሁን ወደ እነርሱ ዘልቆ እየገባ ነበረ። ለዚያች ቀን የተነገረውን ትንቢት ባለመመልከታቸው የማያስተውሉ እንደሆኑ አስቀድሞ ነገራቸው። አሁን ደግሞ ዘልቆ መግባት ጀመረ፡ ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ባለፉት ሁለት፡ ወይም በሦስት ዓመታት ውስጥ የተከናወነውን የዚህን ሁሉ መፈጸም፡ ለዘመኑ የጸናውን ትንቢት ማየት ጀመሩ። የተሰቀለው ወዳጃቸው፡ ኢየሱስ፡ ይህን ቃል እያንዳንዱን እንደ ፈጸመ ያወቁት ያኔ ነበረ። ኦህ፡ ያ ሰው በእውነት ያ መሢሕ እንደ ነበረ፡ እ—እርሱ ከሙታን መነሳት እንደ ነበረበት ያወቁት ያኔ ነበረ። "መቃብር ሊይዘው አልቻለም። 'ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትፈቅድለትም።' ሊወድቅ የሚችል አንድም የትንቢት ቃል የለም። እርሱም በእርግጥ ተነስቷል።"

124 "እንግዲያውስ ዛሬ ጧት በመቃብሩ ዘንድ የነበሩት እነዚያ መልእክተኞች ልክ ነበሩ። ከሙታን ተነስቷል። ሕያው ነው። ያ መሢሕ እርሱ ነው።" አያችሁ? ይህ እንዲያመልጣችሁ። "ድርጊቱ፡ አገልግሎቱና ያደረገው ነገር ሁሉ በዚህ ቀን ይሆናል ብሎ ነቢዩ የተናገራቸውን ቃላት በትክክል ያጸና ነበር። ያ እልባትን ሰጠው።" ያኔ ያንን ያደረገው እርሱ፡ የተሰቀለው ወዳጃቸው፡ ኢየሱስ፡ እንደ ሆነ አወቁ። ሲያነጋግራቸው ልባቸው በውስጣቸው መቃጠሉ አያስገርምም። አሁን ስድስት ማይል ተጓዙ፡ ሆኖም እንደ አጭር ጊዜ ታይቷቸው ነበር።

125 ደግሞም ያደረጉት ሌላ ነገር ይኸውላችሁ፡ ታውቃላችሁ፡ ትንቢት ስለ መጽናቱ የስድስት-ሰዓት ስብከት ሰምተዋል። በመንገድ ላይ የነገራቸው ይህንኑ ነበረ። መንገዳቸውን እንደጀመሩ ወዲያው፡ እርሱ ብቅ አለ፡ ምክንያቱም ልክ እዚያው በኢየሩሳሌም ነበረና። ከስድስት ሰዓት በኋ-... በኋላ፡ ስልሳ ፈርሎንጎች፡ ልክ ስድስት ማይል መንገድ ተጉዘው ኤማሁስ ደረሱ። ይሄው ነው። እርሱም የስድስት ሰዓት የትንቢት መረጋገጥን፡ ሰበከ። እንደዛ ከሆነ፡ በሦስቱ ሰዓቴ እኔን አትኮንኑኝ፡ አያችሁ። አያችሁ? ነገር ግን አስተውሉ፡ እነርሱ ሰበኩ... እርሱ... ትንቢት ስለ መረጋገጡና፡ ስለ መጽናቱ የስድስት-ሰዓት ስብከት አድምጠው ነበር።

126 አሁን ወደ ምሽት ጊዜ እየተቃረበ ነበረ። ታውቃላችሁ፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። በዕብራውያን 13፥8 መሠረት፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ ዓይኖቻቸውን የከፈተው ያኔ ነበረ። በምሽት ጊዜ፡ ነገሮች በትንቢት ግልጽ ይሆናሉ። የዘመኑን ትንቢት ካመናችሁት ብቻ በዚህ ዘመን እየሆነ ያለው ነገር በቀላሉ ሊታወቅ ይችላል።

127 "አዎን፡ እናንተ የማታስተውሉ፡ ለማመን፡ ልባችሁ የዘገየ (በልባችሁ ታወጡታላችሁና ታወርዱታላችሁ)፡ ነቢያት ስለ መሢሑ የተናገሩት ሁሉ፡ መፈጸም አልነበረበትምን?" አሁን እነዚህን ነጥቦች ሁሉ ወደ ኋላ ተመልሶ መረመረና ነቢዩ ይሆናል ያለውን አሳያቸው። ከዚያም ማስተዋል ጀመሩ። ስለዚህ እርሱ... አልፎ የሚሄድ መሰለ። እነርሱም ይህን ሰው ወደዱት። እንዲህም አሉት፡ "አንተ፡ አንተ የሆነ ነገር ሰጥተኸናል። ያንን ፈጽሞ አላሰብንም ነበረ። እርሱ በሆነ ሰፍራ ሕያው ነው።" እርሱንም ያነጋግሩት ነበረ፡ ዳሩ ግን አላወቁትም ነበረ። ስለዚህ እርሱ... ያለ ጥርጥር በሐዘን ተመለከታቸው፡ አልፎም ሊሄድ ጀመረ፡ ነገር ግን እ—እርሱ እንዲጋብዙት ይጠብቅ ነበረ። ዛሬ ማታም የሚጠብቀው ያንን ነው፡ እንድትጋብዙት ነው።

128 አስተውሉ፡ እነዚያ ደቀ መዛሙርት በጠረጴዛው ዙሪያ ወዳለው ኅብረታቸው በጋበዙት ጊዜ፡ ከመስቀሉ በፊት እንዳደረገው የሆነ ነገር ያደረገው ያኔ ነበረ፡ ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ። አያያዙን፡ አደራረጉን ያውቁት ነበረ። ያደረገውንም አወቁ፡ በፊት ያደርግ እንደነበረውም ልክ ያንኑ አደረገ። እነርሱም እንዲህ አሉ፡ "እርሱ ነው!" ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው ሊጮኹ ፈጥነው ተነሱ፡ እርሱም ተሰወረ። ይህን ሰብከት ለማዳመጥ ስድስት ሰዓት የወሰደባቸውን ያህል፡ ምናልባትም በሃያ ደቂቃ ውስጥ በቀልጣፋ-እግር ለሌሎቹ ለመንገር፡ "በእርግጥ ተነስቷል። በእውነት ሕያው ነው" እያሉ ተመለሱ።

129 ወዳጆች ሆይ፡ ይህ የሚልክያስ 4፡ የቅዱስ ሉቃስ 17፡ የቅዱስ ዮሐንስ 15፡ ኦህ፡ እጅግ ብዙ፡ የራእይ 10፡ በትክክል ከዚህ ቀን ጋር ሊጣመሩ የሚችሉ የእጅግ ብዙ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው። እንዲሁም በማርቆስና በማቴዎስ መጽሐፍ ላይ፡ እነዚህ ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች በሰማይ ላይ እንደሚታዩ በተናገረበት፡ ሰዎች ሳውሰርስ፡ በራሪ ሳውሰርስ ብለው የሚጠሯቸው፡ እ—እንደ ሐሳብ ፍጥነትና ኃይል ሊሰወሩ የሚችሉ፡ መንቀሳቀስ የሚችል አእምሮ ያላቸው ናቸው። እርሱ መጻፍ ይችላል፡ መናገር ይችላል፡ የፈለገውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላል። ታላቁ የእሳት ዓምድ፡ "ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።" በምድርም ላይ የሚታዩ እይታዎች፡ የጭስ ፒራሚዶች ወደ አየር ሲወጡ፡ እርጥበትም ሆነ ምንም ነገር ሊኖር ከማይችልበት ከፍታ በላይ፡ ሠላሳ ማይል ከፍ ብሎ እናያለን። ከመሆኑ ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት፡ ልክ እንደዚያ እንደሚሆን ትንቢት ተነግሮ ነበረ። ከዚያም ስዕሉን አዙራችሁ ወደ ታች የሚመለከተው ማን እንደ ሆነ እዩ። ከተነገረው ውስጥ አንዲትም ቃል እንኳ ወድቃ አታውቅም፡ እውነት መሆኑንም የሚያጸናው፡ የእግዚአብሔር የተጻፈ ቃል ይኸውላችሁ። እንደገና የምሽት ጊዜ ነው። ዛሬ ማታ በጸጋው ተመልሶ፡ እዚያ እንዳደረገው፡ አሁን የሆነ ነገር ያደርግ እንደሆን አስባለሁ። እስቲ እንጸልይና እንጠይቀው። በተረጋገጠ ትንቢት ግልጽ የተደረጉ ክስተቶች።

130 ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ፡ እርዳን። ውድ አምላክ ሆይ፡ እንድናስተውል፡ ልናውቃቸው የሚገቡንን ነገሮች እንድናስተውል፡ ቃልህን እንድናስተውል፡ እርዳን። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል ሰብከቶችን፡ የመጻሕፍትን ጽሑፎች ሰምተናል። አሁንም በዚህ በመጨረሻው ዘመን ዳግመኛ ተንሸራትቶ ተመልሷል፡ አሁንም ወደ ምሽት ጊዜ እየተቃረበ ነው። ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሬስባይቴሪያኖች፡ እንዲሁም በዘመናት ውስጥ

ያለፉ ብዙዎቹ ከአንተ ጋር ተነጋግረዋል፡ ምናልባትም ነቢዩ እንዳለው፡ ቀን ወይም ሌሊት ባልሆነው በዚህ ታላቅ ቀን ጉዞ ውስጥ አልፈው ይሆናል፡ ነገር ግን ሲመሽ ብርሃን ይሆናል። ኢየሱስ ከመቃብር ተነስቶ ለስምዖንና ለሴቶቹ ታየ፡ ሕያው እንደ ሆነም አሳያቸው። ያ ጧት ነበረ። ከዚያም በምሽት ዳግመኛ ተመልሶ መጣ። ሆኖም ስለ ዕውርነታቸው እየገሠጻቸው፡ ቀኑን ሙሉ አብሮአቸው ይራመድ ነበረ፡ ዳሩ ግን ሲመሽ ራሱን ለእነርሱ አሳወቀ።

131 አምላክ ሆይ፡ በቃሉ ዙሪያ ወዳለን የዛሬ ማታ ኅብረታችን ና። አምላክ ሆይ፡ ዛሬ በሕዝቦች ዘንድ ይህን ማመን እጅግ ብርቅ ሆኗል፡ ነገር ግን ወደ ዘላለም ሕይወት የጠራሃቸውና የሾምካቸው አንዳንዶች ስላሉ፡ እንዲሁም፡ “አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል” ብለሃልና አመሰግንሃለሁ። አሁንም የምሽት ብርሃናት እያበሩ ባሉበት ጊዜ፡ ጌታ ሆይ፡ (ወደ ፊት ከወጡት መቶዎች ትንቢቶች ውስጥ) አንዲትም ትንቢት እንኳ ለአንድ ጊዜም እንዳትወድቅ፡ አንተ ፈቅደሃል። እንግዲያውስ ይህ በእውነት የሚያጸናው ከሆነ፡ በእርግጥም አንተ መሆን አለብህ፡ ምክንያቱም ማንም ሰው ያን ያህል ትክክለኛ ሊሆን አይችልምና። ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ማንም ሰው በአሥራ ስድስት መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ፡ በአርባ የተለያዩ ጸሐፊዎች፡ ጽፎ፡ አንዳችም ስህተት ሳይኖርበት፡ ሊያደርገው አይችልም።

ውድ አምላክ ሆይ፡ በዕብራውያን፡ 13፥8 መሠረት፡ አንተ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንደ ሆንክ ዛሬ ማታ ራስህን እንድትገልጥ እጸልያለሁ። ያኔ ያደረግኸውን ሥራ፡ ዛሬም ታደርጋለህ። አንተም ተሰፋ ሰጥተሃል፡ “በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ ዓለም እንደ ሰዶምና ገሞራ፡ በጠማማነት በተቀመጠች ጊዜ፡” ብለሃል። እነዚህን ወንዶች ልጆች ልክ እንደ ሴቶች ልጆች ሆነው፡ የሴቶችን ልብስ ለብሰው እናያለን፡ ደ—ደግሞም ሴቶች ልጆች እንደ ወንዶች ልጆች ለመሆን ሲሞክሩ እናያለን፡ በዚህ ጠማማ ዘመንም ያሉትን ሴቶችና ወንዶች ስናይ፡ የፍትወት ስሜት ቀስቃሽነት የ—የአምልኮ ጣዖት ሆኖ እናያለን። ወንጌል ወደ አንድ ወገን ተገፍቶ ወጥቷል፡ በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያንም ዕራቁትነት ሰፍኗል። ኦ አምላክ ሆይ፡ እንዴት ያለ ሰዓት ነው! ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ና፡ ራስህን አሳውቀን። በኢየሱስ ስም እንለምናለንና።

132 አሁን ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ ዓይኖቻችሁንም ጨፍናችሁ ሳለ፡ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እወዳለሁ። እግዚአብሔር እዚህ እንዳለ ታምናላችሁን? እርሱ ዛሬ እያደረገ ያለው ነገር የተፈጸመ ትንቢት እንደ ሆነ ታምናላችሁን? ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንደ ሆነ ታምናላችሁን? እርሱ እዚህ በነበረበትና ለዚያ ዘመን በሥጋ በተገለጠ ጊዜ፡ ያደረጋቸው ሥራዎች በዚህ ዘመን ዳግመኛ እንደሚደገሙ ታምናላችሁን? ነቢዩ እንዲሁ ብሏልና። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ብሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ መፈጸም አለበት፡ ሊወድቅ አይችልም። ራሱን እንዴት አሳወቀ? ሙሴ የተናገረለት ያ ነቢይ በመሆን ነው። የሰዎችን ልብ ምስጢር አወቀ። ሴቲቱ ልብሱን ነካች፡ እርሱም ዘወር ብሎ፡ “እምነትሽ አድኖሻል” አላት። ስምዖን ጴጥሮስ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፡ ስሙን አወቀ፡ እርሱ ማን እንደ ሆነ፡ አባቱ ማን እንደ ሆነ ነገረው። ያው የተወደደው ኢየሱስ አልሞተም፡ እርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕያው ነው። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን! አሁን በዚህ የምሽት ጊዜ፡ እርሱ ዳግመኛ በአንድነት እንደጠራን እምናለሁ።

133 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በመካከላችን ተመላለስ። አትለፈን። ይህ ሌሊት እስኪያልፍ ድረስ፡ መጥተህ ሌሊቱን ሙሉ ከእኛ ጋር እደር፡ ከዚያም ነገ ከአንተ ጋር እንሂድ፡ የትንሣኤህን ኃይል እናውቅ ዘንድ፡ እንዲሁም ፍቅርህ ጸጋህና ምሕረትህ ከእኛ ጋር ይሆኑ ዘንድ። የዘላለም አምላክ ሆይ፡ እነዚህ ነገሮች ይሁኑልን። እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርግልን እንደሚችል እናውቃለን።

134 በዚህ የሰዓቱ ጽሞና ውስጥ፡ ይህንን እንበል። አባት ሆይ፡ አምላካችን፡ ሥጋችን ለአንተ ምስኪን ማደሪያ ነው። ዳሩ ግን፡ ጌታ ሆይ፡ የሚቀድሰው ጸጋህ፡ መንፈስ ቅዱስህ፡ አሁን ይምጣ። ያለአንዳች ጥርጥር ነፃ እንድንሆን፡ በውስጣችን ሊኖር ከሚችል ከማንኛውም ጥርጥርና ግራ መጋባት፡ ከማንኛውም መጠራጠርና ከማንኛውም የጥርጣሬ መስመር አንጻን፥ ወጥተንም፡ ልክ እንደ ጴጥሮስ በድፍረት፡ “አንተ ክርስቶስ ነህ፡ ትናንትና፡ ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነህ፡” ብለን እንድንመሰክር አድርገን።

135 ጌታ ሆይ፡ ቃልህ እውነት እንደሆነ እናምናለን። ጌታ ሆይ፡ ይህን የጸሎት መስመር ከመጀመራችን በፊት፡ እስቲ ራስህን አሳውቀንና፡ ማየት ይሁንልን። አንተ እንዳልከው፡ “በሎጥ ዘመን እንደ ነበረው፡” አብርሃም፡ የተስፋውን ልጅ ሲጠባበቅ የነበረው ያ-የተጠራው ወገን ባለበት፡ እንደ ሕዝብ ሎጥ እዚያ ታች ወርዶ በዚያ የሐይማኖት ተቋም መዋቅር ውስጥ የዘመኑን፡ ቢሊ ግራሃምና ኦራል ሮበርትስን ይሰማ ነበር። ነገር ግን አብርሃም ያለ ምንም ድርጅት መጻተኛ ነበረ፡ ይወርሳት በነበረችው ምድር ውስጥ የሚንከራተቱ ይህ ትንሽ ወገን ብቻ ነበሩ። “የዋሆችም ምድርን ይወርሳሉ።” ከዕለታት አንድ ቀን፡ በዛፍ ጥላ ሥር፡ ተቀምጠው፡ እያረፉ ሳለ፡ እግዚአብሔር በሰው አምሳል ወረደ። ሁለት መላእክት ወደ ሰዶም ወረዱ። እግዚአብሔርም፡ በሰው ሥጋ ሆኖ፡ እርሱነቱን አረጋገጠ፡ እርሱም፡ “አብርሃም፡ ሚስትህ ሣራ፡ የት ናት” አለው? ከዚያ ጥቂት ቀናት በፊት፡ እርሱ አብራም ነበረ፥ እርሷም s-a-r-r-a፡ ሳራ ነበረች፡ ሣራ አልነበረችም፡ ይህም “ልዕልት” ማለት ነው። አንተም በልዕልት ሰሟ፡ በንጉሥ ልጅ ሰሟ ጠራሃት። አብርሃምንም፡ የብዙ አሕዛብ አባት በሚለው ሰሙ፡ አብርሃም ብለህ ጠራኸው። አንተም፡ “እጎበኝሃለሁ” አልከው።

136 አምላክ ሆይ፡ የዚያ ነቢይ ልብ እንዴት ዘሎ ይሆን! በዚያን ጊዜ አንተ ማን እንደ ሆንክ አወቀ። እግሮችህን ማጠቡ፡ የነበረውን ምግብ ሁሉ፡ ደግሞም እጅግ ምርጥ የሆነውን፡ አውጥቶ በፊትህ ማቅረቡ አያስገርምም። እዚያ የነበረው እግዚአብሔር እንደ ሆነ አውቆ ነበር። ከዚያም እንዳላወቀ ሆኖ፡ “ሣራ የት ናት፡” አለው? አንተም...

137 አብርሃምም፡ “በድንኳን ውስጥ... ከአንተ በስተጀርባ፡ በድንኳን ውስጥ ናት” አለው።

138 አንተም ምን እንደሚሆን ተናገርህ። እርሷም፡ በልብዋ፡ ጠረጠረችው። ከዚያም እ—አንተ ለአብርሃም፡ “ሣራ በልብዋ፡ ‘እነዚህ ነገሮች ሊሆኑ አይችሉም’ ብላ፡ ለምን ጠረጠረች? ለእግዚአብሔር የሚሳነው አንዳች ነገር አለን” አልከው?

139 አምላክ ሆይ! ኢየሱስ ሆይ፡ የተገለጠው የቃሉ አምላክ፡ “በሰዶም ዘመን እንደ ነበረው፡” የአሕዛብ ዓለም ከመጥፋቱ፡ የአሕዛብ ዘመን ከመጠናቀቁ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ ዓለም በዚያው ሁኔታ ውስጥ እንደምትሆን

ተናግረሃል። እነሆ እኛ እስከ ወደ ጥልቅ ዘልቀን፡ ሰደማውያን ሆነናል! ከዚያም ሁልጊዜ “ነቢይ፡” ተብሎ የሚጠራው የሰው ልጅ፡ በዚያች ሰዓት እንደሚገለጥ ተናግረሃል። ኦ አምላክ ሆይ፡ ቃላትህን ፈጽም። ጌታ ሆይ፡ የጸሎት መሰመር፡ ሰናደርግ፡ ሕዝቡ ያምኑ ዘንድ፡ እምነትን እንድትሰጠን፡ እነሆ፡ እኛ አማኝ ልጆችህ፡ በቅን ልብ እንጠባበቃለን። አባት ሆይ፡ የምሽት ጊዜ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የምሽት ብርሃናት (የነበረው፡ ያለውና፡ የሚመጣው) በተናገረው ትንቢት ራሱን ይግለጥ። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም። አሜን።

140 አሁን ለታመሙት ለ—ለመጸለይ ዝግጁ ነኝ። ነገር ግን እዚህ ሰንቆም፡ እንዴት ያለ እንግዳ ነገር ነው። እግዚአብሔር አሁንም እግዚአብሔር እንደ ሆነ፡ እዚህ ቆሜ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሰልክ ለተገናኙትና፡ ለሕዝቡ ቻሌንግ እያቀረብኩ እገኛለሁ። ሊወድቅ አይችልም። ተሰፋ የሰጠውንም ነገር፡ ያደርገዋል። ተሰፋ ሰጥቷልና፡ ፈጽሞ ሳያደርገው አይቀርም። ሰለዚህ በተናገረው ቃል ላይ ጽኑ መታመንን ላደርግ እችላለሁ። ሰለዚህ መምጣቱን እጠባበቃለሁ፡ በማንኛውም ጊዜ እንዲገለጥ እጠባበቃለሁ፡ ምክንያቱም፡ “ባላሰባችሁት ሰዓት፡” ዓለም በማያሰበው ሰዓት፡ “ያኔ እርሱ ይገለጣል” ብሏልና።

141 አሁን፡ እሰከማውቀው ድረስ... እዚህ በተበርናክሌ ውስጥ ነኝ፡ የ—የማውቃቸው ጥቂት ሰዎች እዚህ ተቀምጠዋል። ወንድም ራይት፡ እዚህ የተቀመጡት ጥቂቶቹ፡ ልክ እዚህ ያሉትን፡ አውቃቸዋለሁ። ዳሩ ግን የማላውቃችሁ ብዙዎቻችሁ አላችሁ። እግዚአብሔርም ዛሬ ማታ ይህን እንደሚያደርግ የምናገርበት ምንም መንገድ የለኝም። ባለፉት ብዙ ዓመታት ይህን ሲያደርግ አይተነዋል፡ ሆኖም ዛሬ ማታ ላያደርገው ይችላል። አላውቅም። ያ በእርሱ ላይ የተመካ ነው። እርሱ ሉዓላዊ ነው። የፈቀደውን ያደርጋል። ማንም ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው አይችልም። እርሱ በፈቃዱና በመንገዶቹ፡ ብቻውን ይኖራል። ዳሩ ግን ተሰፋ ሰለ ሰጠ፡ እንዲያደርገው እጠይቀዋለሁ። ሰለሚያሰፈልገን ሰለ እኛ ሰንል ሳይሆን፡ ምናልባትም መንፈሰ ቅዱስ እንዲቀባ፡... አሁን በእኛ ላይ ቅባት እንዲወርድ ሰለ አንዳንድ እንግዶች ሰንል ነው። አሁን፡ እኔን ምንም ያህል ቢቀባኝም፡ በእርግጠኝነት፡ እንድታምኑ፡ እናንተንም፡ መቀባት አለበት።

142 አሁን የጸሎት መሰመር እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡ በምችለውም መጠን ለታመሙት መጸለይ እፈልጋለሁ። አሁን፡ ሰዎቹን ጠርተን፡ ወደዚህ ለማምጣት መሰመር ሊኖረን ይችላል፡ የጸሎት መሰመር በማድረግ እዚህ ለታመሙት ሁሉ መጸለይ እንችላለን፡ ብዬ አሰባለሁ፡ አገልጋይ ወንድሞቼን ከእኛ ጋር ወደዚህ እንዲመጡ በማድረግ፡ እጆቻቸውንም እንዲጭኑባችሁ ማድረግ እንችላለን። ያንን በእርግጥ ማድረግ እንችላለን። ወይም ደግሞ ማንኛውንም ነገር ሊያደርግላችሁ ለሚችለው ብቸኛ ለሆነው፡ አባታችን ልንጠይቅ እንችላለን፡ ምክንያቱም እጆቼ ልክ እንደ እናንተ ሰዎች የሰው እጆች ናቸውና። ዳሩ ግን ነገሩ፡ ይህን የሚያደርገው የሰው እጅ አይደለም፥ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በዚያ ቃል ላይ ያለው እምነት ነው ይህን የሚያደርገው። ሰለ እርሱ ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ ነገር የለም፡ ሙሉ በሙሉ ከሳይንስ ውጭ ነው።

143 ክርሰቲያን ባለው የጦር ዕቃ ውሰጥ ሳይንሳዊ የሆነ አንድም ነገር የለም። ያንን ታውቃላችሁን? ፍቅር፡ ደሰታ፡ ሰላም፡ ትዕግሰት፡ ቸርነት፡ የዋህነት፡

ገርነት፡ ጽናት፡ እምነት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ሁሉም ነገር በሳይንስ የማይታይ ነው። እውነተኛና ዘላቂ የሆነውም ብቸኛው ነገር ያ ነው። የምትመለከቱት ነገር ሁሉ ከምድር መጥቶ ወደ ምድር ይመለሳል። ዳሩ ግን በዓይናችሁ ልታዩዋቸው የማትችሏቸው፡ ሆኖም ራሱን ሲገልጽ የምታዩት ነገሮች፡ ያ የዘላለም ዓለም ነው።

144 ከዚህ መልእክት በኋላ፡ እግዚአብሔር ራሱን ቢገልጥና እርሱ እዚህ ሕያው እንደ ሆነ፡ በመጀመሪያ ያደርጋቸው የነበሩትን ያው ነገሮች እያደረገ፡ ራሱ እንደሆነ ቢያሳይ፡ ይህን እንደ ፈውሳችሁ አድርጋችሁ ትቀበሉታላችሁን? እግዚአብሔር ያድርግልን። አሁን በቤቱ ውስጥ ያላችሁትን ማንኛውንም ሰው፡ ማንኛውም ብትሆኑ ወይም ከየትም ብትመጡ፡ ይህን መልእክት እውነት እንደ ሆነ አጥብቃችሁ እንድታምኑ እጠይቃችኋለሁ። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህች ሰዓት ያለው መልእክት ያ ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ማታ እዚህ እንዳለና ሕያው እንደ ሆነ። አሁን ወደ...

145 ሁላችሁም ስለ እኔ ታውቃላችሁ፡ ያደግሁት ልክ እዚሁ ከተማ ውስጥ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንኳ የለኝም። ያ በትክክል እውነት ነው። ደግሞም ለረጅም ጊዜ ታውቁኛላችሁ፡ እኔ ታማኝና ቅን መሆኔን ላሳያችሁ በፊታችሁ እንደ ኖርኩ ተሰፋ አደርጋለሁ። ግብዝ አይደለሁም። ነቃፊዎቼ እንኳ ያንን አይሉም። እነርሱ፡ እነርሱ እንዲህ ብቻ ይላሉ፡ “እ—እንተ ግብዝ አይደለህም፡ ነገር ግን እንዲሁ ተሳስተሃል። ሆነ ብለህ ሳይሆን፡ ባለማወቅ ተሳስተሃል።” የእግዚአብሔር ቃል ለመልእክቴ ስለሚመሰክር፡ እርሱም ማን እንደ ሆነ ሊነግራችሁ ስለሚገባ፡ ባለማወቅ የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ደግሞም እኔ እንዳልሆንኩ በግልጽ ሰናገር ትሰሙኛላችሁ፡ እንግዲያውስ እርሱ መሆን አለበት። ልክ ነውን? እንግዲያውስ በእግዚአብሔር እመኑ። ወደዚህ ተመልከቱና፡ በእግዚአብሔር እመኑ። በእግዚአብሔር ማመን ከቻላችሁ፡ እግዚአብሔር ይሰጣችኋል። በፊት እንዳደረገው አሁንም ያንን ማድረግ ከቻለ፡ እንግዲያውስ አሁንም እግዚአብሔር ነው። ያንን ታምናላችሁን?

146 ታምኑታላችሁን? እዚህ በፊቴ የተቀመጠች አንዲት ሴት፡ በእንባ በተሞሉ ዓይኖች፡ በቅንነት፡ ትመለከተኛለች። ማን እንደ ሆነች አላውቅም፡ ፈጽሞ አይቻት አላውቅም። እኔም ለአንቺ እንግዳ ነኝ። እግዚአብሔር የልብሽን ምስጢር፡ ፍላጎቶችሽን፡ ወይም ኃጢአትሽን፡ ወይም ምንም ይሁን ምን ያውቃል ብለሽ ታስቢያለሽን? የሚያውቅ ይመስልሻልን? ኃጢአትሽ ምን እንደ ሆነ፡ ምን እንዳደረግሽ፡ ማድረግ ያልነበረብሽን ነገር፡ ወይም ፍላጎትሽ፡ ምንም ይሁን ምን? ይህን ቢያደርግ፡ በእርሱ እንድታምኚ ያደርግሻልን፡ ያ እርሱ መሆኑን ታውቂያለሽን? እርሱ እንደ ሆነ አድርገሽ ትቀበይዋለሽን? እያስጨነቀሽ ያለው ኃጢአትሽ አይደለም፥ ያንን ተናዝዘሻል። ዳሩ ግን የእርሱን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እየፈለግሽ ነው። ትቀበይዋለሽ። በእርሷ ላይ ወርዶ ሲያልፍ አይቻለሁና።

147 ሴቲቱን እመለከት እንደነበር፡ እርሷም ትመለከተኛ እንደነበር እንድታውቁ፡ መንፈስ ቅዱስን ላሳያችሁ እወዳለሁ። እዚህ ተመልከቱ፡ ልክ እዚህ የተቀመጠችው ይህች ሴት ላይ፡ እዚህ ከእግሬ ሥር በታች። ያንን ሰናገር፡ እርሷ የምትፈልገውም ተመሳሳይ ነው፡ እርሱም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። እኅቴ ሆይ፡ እንደምትቀበይው ታምኚያለሽን? እንግዲያውስ፡ እጅሽን አንሺ። እስከማውቀው ድረስ፡ ይህችን ሴት በሕይወቴ ፈጽሞ አይቻት አላውቅም።

148 እዚህ ራሱን ዝቅ አድርጎ የተቀመጠውን፡ ልክ እዚያ የተቀመጠውን፡ ኮሌታው ያልተስተካከለለትንና፡ የመሳሰለውን ይህን ሰው ታያላችሁን? በፊኛ በሽታ ትሰቃያለህ። እግዚአብሔር እንደሚፈውስህ ታምናለህን? የምትቀበለው ከሆነ እጅህን አንሳ። መልካም፡ እግዚአብሔር ጥያቄህን ይሰጥህ።

149 ልክ እዚህ የተቀመጠው ይህ ወጣት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ይፈልጋል። ነጭ ቀጭን ክራባትህን ወደ ኋላ ያንጠለጠልከው፡ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ ታምናለህን? እግዚአብሔር ያደርገዋል።

150 እዚህ ያለው ይህ ሰው ለሚስቱ እየጸለየ ነው። እርሷ በሕክምና ተቋም ውስጥ ናት። እግዚአብሔር እንደሚፈውሳትና ጤናማ እንደሚያደርጋት ታምናለህን? ታምነዋለህን? መቀበል ትችላለህ።

151 እጅሽን ወደ ጉሮሮሽ እንዳነሳሽ፡ እግዚአብሔር እያስቸገረሽ ያለውን ያንን የልብ ሕመም፡ ያለብሽን ያንን የጨጓራ ሕመም ሊፈውሰው እንደሚችል ታምኚያለሽን? አሁን እየተሰቃየሽ፡ እዚያ ተቀምጠሻል። ልክ ነውን? እርሱ እንደሚፈውስሽ ታምኚያለሽን? እንግዲያውስ ልታገኚው ትችያለሽ። አሜን።

152 እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንደ ሆነ እያችሁ። እነዚያን ሰዎች ጠይቋቸው፡ እኔ አውቃቸው እንደሆነም እዩ። እኔ አላውቃቸውም፡ እርሱ ግን ያውቃቸዋል። አሜን። እዚያ ግድግዳው አጠገብ ወዲያ ያለውን ያንን ብርሃን እያችሁ፡ እዚያ በተቀመጠው ሰው ላይ ልክ ወደ ታች ተንጠልጥሎ። እርሱ በጀርባው ላይ ባለው የአከርካሪ አጥንት ሕመም ይሰቃያል። እርሱ ከዚህ አይደለም፡ ከጆርጂያ ነው። አቶ ደንካን፡ በሙሉ ልብህ እመን፡ እግዚአብሔር ያንን የጀርባ ሕመም ይፈውሰዋል። በሙሉ ልብህ ታምናለህን? እግዚአብሔር ይባርክህ።

153 የጀርባ ሕመም ያለበት፡ እኔን የሚመለከት፡ አንድ ሰው እዚህ ኋላ ተቀምጧል። እኔ አላውቀውም፡ እርሱ ግን አቶ ቶምፕሰን ነው። ታምናለህን? ወዳጄ ሆይ፡ እዚያ ኋላ፡ ተነስ፡ ስለዚህ... እኔ ለአንተ እንግዳ ነኝ። ልክ ነው። ዳሩ ግን እዚያ ተቀምጠህ፡ እየጸለይህ ነው። አሁን የጀርባ ሕመምህ ተፈውሷል። ኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ ያደርግሃል።

154 "በምሽት ጊዜ ብርሃን ይሆናል።" እያችሁም አይደል? እርሱ ዛሬ ማታ እዚህ አለ! እርሱ **ታላቁ እኔ ነኝ** ነው። እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። ታምኑታላችሁን? ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን እያሳወቀ፡ ራሱን በትንቢት ውስጥ እየገለጠ እንደሆነ ረክታችኋልን አምናችኋልን?

155 ስለ ዓይንህ አትጨነቅ። እግዚአብሔር የታመሙትንና የተሰቃዩትን ይፈውሳል።

156 ስንት ሰዎች... እዚህ ውስጥ የታመሙ ስንት ናቸው? እስቲ እጆቻችሁን ልይ። ዝም ብሎ እንደ ታላቅ ስህበትና ጫና ሆኖ ይሰማኛል። ከእናንተ ውስጥ የጸሎት ካርድ ያላችሁ አላችሁን? እንዴት አድርጌ ወደዚህ ላሳልፋችሁ እንደምችል አላውቅም። ልጸልይላችሁ እፈልጋለሁ፡ ዳሩ ግን እንዴት እንደማደርገው አላውቅም። ምን እንደሆነ እያችሁ፡ ግድግዳውን ተመልከቱ፡ እንዴት አድርጌ ወደዚያ ላስገባቸው እችላለሁ? የአንዱን መተላለፊያ መንገድ ብታጨናንቁትስ ምን ይሆናል? ሌላኛውን ልክ እዚያው ዘግታችሁታል፡ እያንዳንዱ ሰው በቆመበት ቆሟል።

157 አድምጡ፡ ስሙኝ። እስካሁን በጌታ ስም ነግሬያችሁ ያልተፈጸመ አንዳች ነገር አለን? ልክ ነውን? ሁልጊዜም ሁሉም ነገር ትክክል ነበረ። በሕይወቴ አንድ ሳንቲም እንኳ ጠይቄያችሁ፡ አውቃለሁን? አንዴም እንኳ። በሕይወቴ መባ ወሰጄ አላውቅም። እዚህ ያለሁት ለገንዘብ አይደለም። እዚህ ያለሁት እናንተን ለማታለል አይደለም። እዚህ ያለሁት የእግዚአብሔርን የዘመኑን ቃል ልገልጥ ነው። እውነቱን ነግሬያችኋለሁ፡ እግዚአብሔርም እርሱ እውነት እንደ ሆነ መሰክሯል። አሁን እላችኋለሁ፡ **መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ**፡ አማኝ በታመሙት ላይ እጆቹን ቢጭን፡ ኢየሱስ፡ "ይድናሉ" ብሏል! ያንን ታምናላችሁን? እንግዲያውስ፡ በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ሆኖ፡ አሁን እንደሚያደርገው አታምኑምን?

158 አሁን እርስ በርሳችሁ እጃችሁን ተጫጫኑ፡ ለአንድ ደቂቃም ያህል እዚያው አቆዩት። አሁን፡ አ—አትጸልዩ፡ ዝም ብላችሁ እርስ በርሳችሁ እጃችሁን ተጫጫኑ፡ እዚያ ውጭ በየቦታው ያላችሁም። እኔም፡ ራሴ፡ በእነዚህ መሀረቦች ላይ እጄን እጭናለሁ። አሁን ለአንድ ደቂቃ ያህል እኔን እንድትመለከቱኝ እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር ሳያደርገው የተወው ምን ነገር አለ? እርሱ እንዴት እንደሆነ ተመልከቱ፡ ያነበብነው ቃል ምን እንደሆነ፡ የተናገርናቸው ትንቢቶች፡ ኢየሱስ ራሱን በትንቢቶች እንደለየ። አሁን ዘመኑን ተመልከቱ፡ እንዲሁም በዚህ ባለፉት ሦስት ሳምንታት ውስጥ እኛ የምንኖርበትን ዘመን ያስቀመጥንበትን ቦታ ተመልከቱ። የተመረጡትን የሚያስቱ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና ሊታዩ ስለተቃረቡ ምልክቶች፡ ያነበብነውን ተመልከቱ። ቃሉ እንዴት እንደ ተገለጠ፡ የዚህ ዘመን አምላክ የሰዎችን ውሸት... ልብ እንዴት እንዳሳወረ። እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱ በትንቢቶቹ በኩል እነዚህ ነገሮች በዚህ የሎዶቅያ ዘመን እንደሚፈጸሙ እንዴት እንደ ተናገረ። ምንም ሳይደረግ የቀረ ነገር የለም። በኤማሁስ ከነበሩት እነዚያ ሰዎች ጋር የተነጋገረው ያው አምላክ ልክ እዚህ አለ፡ ስለ እርሱ አስቀድመው በተነገሩት ትንቢቶች ራሱን እንደገለጠ ሁሉ፡ እርሱ ዛሬ ማታም ለዚህ ዘመን አስቀድመው በተነገሩት ትንቢቶች ህልውናውን እየገለጠ እዚህ ይገኛል። እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። ልታምኑት ትችላላችሁን? እንግዲያውስ እርስ በርሳችሁ እጃችሁን ተጫጫኑ። ለራሳችሁ አትጸልዩ፡ ዳሩ ግን እጃችሁን በጫናችሁበት በዚያ ሰው ላይ በራሳችሁ መንገድ ጸልዩለት፡ ምክንያቱም እነርሱ ለእናንተ እየጸለዩላችሁ ነውና። አሁን ተመልከቱ፡ አትጠራጠሩ።

159 አሁንም እኔ የምመለከተውን ልታዩት ብትችሉ ኖሮ! ደግሞም እዚህ ቆሜ፡ እንደማልዋሻችሁ ታውቃላችሁ። ልታዩት ብትችሉ፡ እንዲሁም ሳይንስ ፎቶግራፉን ያነሳውን እዚያ ወዲያ በ—በአየር ላይ የተንሳፈፈውን፡ ያንን ታላቅ መንፈስ ቅዱስ እምነታችሁ ሊሰበው ቢችል ኖሮ፡ የ—የሚያርፍበትን ስፍራ ለማግኘት፡ መልህቅ የሚጥልበትን ስፍራ ለማግኘት እየሞከረ በዚህ ሕንፃ ውስጥ ሲንቀሳቀስ ታዩት ነበር። ወንድሜ ሆይ፡ እመነው ብቻ። ልክ እንደሆነ፡ በመጽሐፍ ቅዱስና በመሳሰሉት ነገሮች ገልጦታል። አሁን እጃችሁን ለጫናችሁበት ለዚያ ሰው በቅንነት ጸልዩለት፥ እነርሱ ለእናንተ እየጸለዩላችሁ ነው።

160 ውድ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፡ በእርግጥ፡ ጌታ ሆይ፡ በቃሉ አማካኝነት፡ እዚህ እንዳለህ፡ እናውቃለን፥ በተሰፋ ቃልህ መሠረት አንተ እዚህ እንዳለህ፡ "ሁለት

ወይም ሦስት በሰሜ በሚሰበሰቡበት፡ በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፥ በድውዮች ላይ እጃቸውን ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ" ብለሃል። ታላቁ መንፈስ ቅዱስ፡ በዚህ የሰልክ ሞገድ ላይ አቋርጦ ወደ እያንዳንዱ ጉባኤ ይግባ። ልክ እዚህ በቤተ ክርስቲያኒቱ የምንመለከተው ያው ቅዱስ ብርሃን፡ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ይውረድ፡ በዚህም ጊዜ ይፈወሱ። የክርስቶስ ህልውና ባለበት ጠላትን፡ ዲያብሎስን እንገሥጸዋለን፡ ጠላትን እንዲህ እንለዋለን፥ እርሱ በጌታ ኢየሱስ ቤዛዊ መከራና ሞት፡ እ—እንዲሁም በሦስተኛው ቀን በድል አድራጊው ትንሣኤ ተሸንፏል፡ ከነዚህ ከአሥራ ዘጠኝ መቶ ዓመታት በኋላ አሁንም ሕያው ሆኖ፥ እዚህ በመካከላችን እንዳለ በሚያሳየው፡ የተረጋገጠ ማስረጃው፡ ተሸንፏል። ህያው የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ የእያንዳንዱን ልብ በእምነትና በኃይል፡ እንዲሁም አሁን በህልውናው በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ በሚያንዣብበው በዚህ ታላቅ ብርሃን፡ በተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የፈውስ ኃይል፡ ይሙላው። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁንልን።

161 የጸለይንባቸው እነዚህ መሀረቦች፡ የታሰቡላቸውን የታመሙትንና የተሰቃዩትን ለማዳን ይድረሱ። አሁን እዚህ ራሱን እየገለጠ ያለው ያው መንፈስ ቅዱስ፡ እነዚህ መሀረቦች በሚጫኑበት እያንዳንዱ በሽተኛ ላይ ራሱን ይግለጥ። የሰውነታቸው ሕመም እስኪፈወስ ድረስ የእግዚአብሔር ህልውና ልባቸውን በእምነት ይሙላው። የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች እንደ መሆናችን፡ ይህንን የምንለምነው፡ ለእግዚአብሔር ክብር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ህልውና ፊትና በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ነው። አሜን።

162 አሁን ከልባችሁ፡ ምንም ዓይነት ሕመም ቢኖርባችሁ፡ ምንም አይገደኝም፡ ከልባችሁ፡ የእግዚአብሔር ቃል ልመናችሁን እንደመለሰላችሁ በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ? ማየት እንደቻልኩት፡ እያንዳንዱ እጅ፡ ወደ ላይ እንደ ተነሳ አምናለሁ። የምታምኑ ከሆነ፡ አሁን አስታውሱ፡ ተፈጽሟል።

163 እዚያ ውጭ በሰልክ መሰመሮች ላይ ያላችሁ እናንተም፡ አገልጋዮችና፡ ወዳጆቻችሁ እጆቻቸውን ሲጭኑባችሁ፡ በሙሉ ልባችሁ ካመናችሁ፡ እንደ ተፈጸመ በሙሉ ልባችሁ ካመናችሁ፡ በእርግጥ ተፈጽሟል። ታላቁ መንፈስ ቅዱስ፡ ዛሬ ማታ እዚህ በተበርናክሉ ውስጥ ይገኛል። እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን ለማሳየት፡ የልብን ምስጢር በመግለጥና፡ የህልውናውን በመግለጥ በማሳየት፡ በሕዝቡ ላይ ሲንቀሳቀስ፡ እዚህ ግድግዳው አጠገብ ራሱን ሲያሳይ፡ ደግሞም በአንድ ሰው ላይ ሲወርድ፡ ወደዚህ ሲመጣና፡ በሕንፃው ውስጥ ሲያልፍ አይቻለሁ። እርሱ በመካከላችን ነው! እርሱ ፈጽሞ-የማይወድቅ አምላክ፡ እግዚአብሔር ነው።

164 ልባችን በውስጣችን አልተቃጠለምን፡ አሁንም ቢሆን፡ ክብርና ምስጋና ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ይሁንና፡ አሁን ከሙታን በተነሳው በኢየሱስ ክርስቶስ ህልውና ፊት መሆናችንን ማወቃችን ልባችንን እያቃጥለውምን፥ ሁሉን ቻዩ የይሖዋ ትክክለኛ ምሳሌ የሆነው፥ የአንድን ነቢይ ትኩረት ለመሳብ፡ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ በእሳት ዓምድ አምሳል የተንሳፈፈውና የወረደው፥ በተራራው ላይ የወረደው፡ ከሙሴና ከኢያሱ በቀር፡ የነካው ማንም ሰው ይገደል ዘንድ የነበረው እርሱ፡ ዛሬ ተለይተው ለተጠሩት ሕዝቦች እንደ

ጥላ ሆኖ፡ የእስራኤልን ልጆች በጉዞአቸው፡ በምድረ-በዳ ውስጥ እንዴት እንደመራቸው እናውቃለን። ይኸውና እርሱ፡ በሳይንሳዊ ምርምር፡ በሳይንስ ፊት እንኳ ሳይቀር ራሱን ገልጧል። እርሱ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን በማሳየት፡ በትክክለኛው ድርጊቱና በትክክለኛው ትንቢቱ፡ እርሱ በዚህ ዘመን፡ ያደርጋቸዋል ተብለው ትንቢት የተነገረላቸው ነገሮች፡ ፍጹም በሆነ ሁኔታ፡ የጸኑ ሆነዋል። ይህ ልባችን በውስጣችን እንዲቃጠል ለማድረግ በቂ አይደለምን? እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

165 አሁን በአንድ ልብ፡ ቆመን እንዲህ እንበል፥ “አሁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኜና እንደ ፈዋሼ እቀበላለሁ። ደግሞም በጸጋው፡ ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ወደ ፊት፡ ኦ አምላክ ሆይ፡ የዚህ ዘመን ትንቢት ሲፈጸም አይቻለሁና፡ ማናቸውም አለማመን ከእንግዲህ በልቤ ውስጥ አይግባ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው እንደ ሆነና የዚህ ዘመን ቃሉን እያረጋገጠ አሁን እዚህ እንዳለ አምናለሁ። ስለ እርሱ የተጻፉት ትንቢቶች አሁን በመካከላችን ተፈጽመዋል። እርሱ አዳኜ፡ አምላኬ፡ ንጉሤ፡ የእኔ ሁሉ-በ-ሁሉ ነው።”

166 ውድ አምላክ ሆይ፡ ምስክርነታችንን ሰማ። ዕለት ዕለትም፡ የሕይወትን እንጀራ፡ ሰጠን። አምላክ ሆይ፡ ከልባችን ጥልቅ፡ ምስጋናን እናቀርብልሃለን። ኃያል የሆንከው፡ የነቢያት አምላክ ሆይ፡ አንተን እናመሰግንሃለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም። አሜን።

ኦ! እንዴት ሁኔታ፡ እንዴት ያለ ጊዜ ነው!

> … እመን ብቻ፥
> እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፡
> ሁሉም ነገር ይቻላል፡ እመን ብቻ።

እንዲህ እንዘምር።

> አሁን አምናለሁ፡ ኦህ፡ አሁን አምናለሁ፡
> ሁሉም ነገር ይቻላል፡ አሁን አምናለሁ፥
> አሁን አምናለሁ፡ ኦህ፡ አሁን አምናለሁ፡
> ሁሉም ነገር ይቻላል፡ አሁን አምናለሁ።

ይህ ምስክርነታችሁ ነውን? አሁን ራሳችንን ዝቅ እንዳደረግን፥

> እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
> በኢየሱስ እግር ስር እስክንገናኝ፥
> እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
> እንደገና እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

[ወንድም ብራንሃም **እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን** የሚለውን አዜመ—እርታዒ።] (የምትለው ነገር አለህ? ቬይል።)

> … ኢየሱስ እግር አጠገብ፥
> እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
> እንደገና እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

167 ራሳችንን ዝቅ እንዳደረግን፡ ወንድም ቬይል በጸሎት ሊያሰናብተን እዚህ ቆሟል። ወንድም ሊ ቬይል፡ እዚህ ለታበርናክሉ ጽሑፎችን፡ መጻሕፍትንና፡ የመሳሰሉትን የሚጽፍ ወንድም ነው። በጣም ውድ ወንድም ነው፡ በብዙ

የወንጌል ዘመቻዎች ከእኔ ጋር አብሮ ሆኗል። እያንዳንዱን አገልጋይ፡ እዚህ ጋብዜ ላነጋግራቸው ዕድሉን ባገኝ እመኛለሁ። እንደምትረዱኝ፡ እርግጠኛ ነኝ። ሁላችሁም አገልጋዮች፡ እዚህ በመገኘታችሁ ደስ ብሎናል። ምዕመናን ሁላችሁ፡ ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የመጣችሁ ሰዎችና፡ ሌሎችም-ሁሉ፡ እዚህ በመገኘታችሁ ደስ ብሎናል። እርስ በርሳችንም በእውነት ጸሎታችን፡ “ዳግም እስከምንገናኝ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን” የሚለው ነው። ራሳችንን ዝቅ አድርገን፡ እጃቻችንንም አንስተን፡ በድጋሚ ለእግዚአብሔር እጅግ በሚያምር በሚጣፍጥ ሁኔታ እንዘምረው።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
በኢየሱስ እግር ስር እስክንገናኝ!
እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
እንደገና እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

65-0801E በትንቢት ግልጽ የተደረጉ ክስተቶች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org